# አዲስ ዘመን

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 225 ሚያዝያ 15 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# «ጀኔራል ሰዓረ ለኢትዮጵያ ወታደሮችና ለትውልድ የአገር ወዳድነትና የጀግንነት ተምሳሌት ነው»

- ወ/ሮ አዳነች አቤቤ
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጀኔራል ሰዓረ ለኢትዮጵያ ወታደሮችና ለትውልዱ የአገር ወዳድነትና የጀግንነት ተምሳሌት ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ። የጀኔራል ሰዓረ መኮንን መታሰቢያ ፓርክና ሐውልት የክብር እንግዶች በተገኙበት ትናንት በአዲስ አበባ ተመርቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዚህ ጊዜ እንደገለጹት፤ ጀኔራል ሰዓረ የተሰዋው ለአገሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለኢትዮጵያ ወታደሮችና ለትውልዱ ተምሳሌት ነው። አሟሟቱ ቢያሳዝነንም ጀኔራል ሰዓረ የሞተለት ዓላማ የመከላከያ ሠራዊቱ ማስተማሪያ ሆኖ መቀጠሉን ተናግረዋል።

የጀኔራሉ ሐውልት አዲስ አበባ ላይ የተገነባውም የጀኔራሉን ወታደራዊ ታሪክ ማስተማሪያ ለማድረግ ነው ብለዋል። በስሙ በተሰየመ ፓርክና ሐውልት ብቻ ሳንወሰን ወጣቶች ከጀኔራሉ የሕይወት ታሪክ የሚማሩበትን ሥራ በቀጣይነት ከተማ አስተዳደሩ ይሠራል ነው ያሉት።

የመከላከያ ሚኒስትር ዶክተር አብርሃም በላይ በሥነሥርዓቱ

«ጀኔራል ሰዓረ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










ወይዘሮ አይሻ መሐመድ

# ክልሉ

## ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች ፈቃድ ሰጥቷል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስምንት ወራት ከአራት ቢሊዮን 323 ሚሊዮን በላይ ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠቱን የአፋር ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ።ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በክልሉ በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ላይ ከፍተኛ መነቃቃት መታየቱ ተጠቁሟል።

ክልሉ ከአራት ቢሊዮን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ለኩላሊት ሕክምና

## በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱ መቸገራቸውን ታካሚዎች ገለጹ

### - ጤና ሚኒስቴር አገልግሎቱን ለማሻሻል እንደሚሠራ አስታውቋል

**መስከረም ሰይፉ**



አዲስ አበባ፡- ለኩላሊት በሽታ የሚሰጠው ትኩረት እጅግ አናሳ በመሆኑ በሕክምና ተቋማት በቂ ሕክምናና የመድኃኒት አቅርቦት እያገኘን አይደለም ሲሉ የኩላሊት በሽታ ታካሚዎች ገለጹ።የጤና ሚኒስቴር በበኩሉ አገልግሎቱን ለማሻሻል ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን አስታውቋል።

የኩላሊት ታማሚ ሆኖ ዲያሊሲስ ከጀመረ አንድ ዓመት ከ6 ወር የሆነው ወጣት አቶ ሁሴን አሊ እንደገለጸው፤ የኩላሊት ሕመም ሲያጋጥም ፈተናዎቹ በርካታ ናቸው።ምንም እንኳን የጳውሎስ አጠቃላይ ሆስፒታል የኩላሊት ንቅለ ተከላ ሕክምና መስጠት ከጀመረ ዓመታት ቢቆጠሩም አሁንም በርካታ ታማሚዎች ወደ ውጭ አገር ሄደው እየታከሙ ነው።ውጭ አገር ሄደው ሕክምናውን ለማግኘት ጎዳና ላይ ወጥተው የሚለምኑም በርካቶች ናቸው።

«እኔ የኩላሊት ንቅለ ተከላ ማድረግ እንዳለብኝ በሕክምና ባለሙያዎች በተነገረኝ ጊዜ የጳውሎስ አጠቃላይ ሆስፒታል በኮቪድ 19 ምክንያት የኩላሊት ንቅለ ተከላ ሥራ አቁሞ የነበረ በመሆኑ ወደ ውጭ አገር ሄዶ መታከም ግድ ሆኖብኝ ነበር» የሚለው አቶ ሁሴን፤ ውጭ አገር ሄዶ ለመታከም አቅሙ ስለማይፈቅድለት ንቅለ ተከላውን ለማድረግ ጎዳና ላይ ወጥቶ የሕክምና ወጪውን ማሰባሰብ መጀመሩን አስታውሷል።

አቶ ሁሴን ዕድል ቀንቶት ለሕክምና የሚያስፈልገውን ብር አግኝቶ በ16 ሺ ዶላር ቱርክ አገር ካለ ሆስፒታል ጋር ተነጋግሮ ገንዘቡን አስገብቶ ንቅለ ተከላውን ለማድረግ ወደ ቱርክ አቀና።ሕክምናውን አድርጌ እመለሳለሁ ብሎ ከአገሩ የወጣው ሁሴን ኩላሊት ከምትሰጠው እህቱ ጋር ቪዛው ላይ ያለው የዕድሜ ልዩነት የስድስት ወር ብቻ

ለኩላሊት ሕክምና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኦሮሚያ ክልል

## ለአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር 12ሺህ ኩንታል የችግኝ ዘር አሰራጭቷል

ገጽ 4



# በሶማሌ ክልል ከ593 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት እየለማ ነው

## - ከበልግ ግብርና 20 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- የወቅቱን ዝናብ በመጠቀም ከ593 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት እየለማ መሆኑን የሶማሌ ክልል አስታወቀ። ከበልግ ግብርና ሥራዎችም ከ20 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡

የሶማሌ ክልል የግብርና ቢሮ የሰብል ልማትና ጥበቃ ዳይሬክተር አቶ አብዲ አደን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የወቅቱን ዝናብ በመጠቀም በተለያዩ አካባቢዎች የግብርና ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

ለማልማት ከታቀደው 593 ሺህ 324 ሄክታር መሬት 20 ሚሊዮን 197 ሺህ 712 ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡ በክልሉ ከፍተኛ የሆነ የአርሶ አደሮች ንቅናቄ በማድረግ የታቀደውን ለማሳካት ጥረት ይደረጋል ያሉት አቶ አብዲ፤ በአሁኑ ወቅት በከፊል አርሶ አደር አካባቢዎች የተለያዩ ሰብሎች እየተዘሩ መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በዘንድሮው ዓመት በክልሉ በዋናነት የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የማሽላ፣ የበቆሎና የስንዴ ልማት እየተከናወነ ይገኛል። በክልሉ የተያዘውን ወር ጨምሮ በሁሉም ዞኖች ላይ ዝናብ በመዝነብ ላይ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ለአርሶ አደሩ ምርጥ ዘር የማቅረብ ሥራ በመሠራት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከ12 ሺህ 608 በላይ ኩንታል የማሽላ፣ ስንዴና የበቆሎን ጨምሮ የተለያዩ ምርጥ ዘር ተዘጋጅቷል። 3 ሺህ 928 ኪሎ ግራም የአትክልት ዘርና ችግኝ በቢሮ ደረጃ በመዘጋጀት ላይ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ከፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ከ9 ሺህ 700 ኩንታል በላይ ምርጥ ዘር የሚጠበቅ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የአፈር ማዳበሪያ በተገቢው ጊዜ ለማቅረብ ዝግጅት ተደርጓል ያሉት አቶ አብዲ፤ 4 ሺህ 800 ኩንታል ማዳበሪያ ተዘጋጅቷል፤ 2 ሺህ 400 ኩንታል ማዳበሪያ በተጨማሪነት ማዘጋጀት ያስፈልጋል ሲሉ አስታውቀዋል።

በመስኖ አካባቢዎች ለአርሶ አደሮች አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ 272 የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን ለማሰራጨት እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል። በአሁኑ ወቅት ላይ በክልሉ ያለው የዝናብ ሁኔታ ጥሩና ለሰብል ልማት አመቺ ነው፡፡ በዚህም የክልሉን አርሶ አደር ኅብረተሰብ የመቀስቀስና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ በመሠራት ላይ ይገኛል ብለዋል።

በክልሉ የሰብል ልማት በፋፈን አካባቢ ስንዴ፣ በቆሎና ማሽላ በይበልጥ መልማት የሚያስችል መሆኑን ጠቁመው፤ ሸበሌና አፍዴር አካባቢዎች ላይ በአብዛኛው የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን በመጠቀም የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በመስኖ እንደሚለማባቸው ገልጸዋል።

በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ላይ በመስኖ የማልማት ሥራ በመሠራት ላይ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ በሊበን ዞን በሦስት ወረዳዎች ስንዴ እየለማ መሆኑን አስታውቀዋል።

በባለፈው ዓመት በክልሉ ከ119 ሺህ 688 ሄክታር መሬት ላይ ከ9 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአትክልት ምርት ተገኝቷል ያሉት አቶ አብዲ፤ በ609 ሺህ 745 ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የሰብል ምርቶችን በማልማት ከ12 ሚሊዮን 279 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰብ እንደተቻለ ጠቁመዋል።



አምባሳደር መለስ ዓለም

# አንዳንድ የመገናኛ ብዙኃን በሱዳን ችግር የኢትዮጵያ ጣልቃገብነት እንዳለ አስመስለው የሚያናፍሱት መረጃ መሠረተ ቢስ ነው

## - የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አንዳንድ የመገናኛ ብዙኃን በሱዳን ግጭት የኢትዮጵያ ጣልቃገብነት እንዳለ አስመስለው የሚያናፍሱት ሀሰተኛ እና መሠረተ ቢስ መረጃ ችግሩን አካባቢያዊ ለማድረግ ከሚመነጭ ፍላጎት የተነሳ እንደሆነ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። መንግሥት በሱዳን የሚገኙ ዜጎቻችንን ሁኔታ እየተከታተለ መሆኑን ሚኒስቴሩ አረጋግጧል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም ወቅታዊውን የሱዳን ሁኔታ አስመልክቶ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያና ሱዳን በመንግሥታት መለዋወጥ ያልዋዠቀ ጽኑ ወዳጅና ጎረቤት አገራት ናቸው፡፡ ሱዳን ካጋጠማት ወቅታዊ ፈተና እንድትወጣ ኢትዮጵያ በየትኛውም ሁኔታ ከሱዳናውያን ጎን መሆኗን ታረጋግጣለች።

ያም ሆኖ አንዳንድ መገናኛ ብዙኃን በግጭቱ የኢትዮጵያ ጣልቃገብነት እንዳለ አስመስለው የሚያናፍሱት መረጃ የሁለቱን አገራት ታሪካዊ ወዳጅነት የማይመጥን መሠረተ ቢስና ሀሰተኛ መሆኑን ተናግረዋል። ይህን ሀሰተኛ መረጃ የሚያሰራጩ አካላት በሱዳን የተፈጠረውን ችግር አካባቢያዊ ከማድረግ የመነጨ ፍላጎት መሆኑን ነው የገለጹት።

የኢትዮጵያ መሪዎች ከቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ጀምሮ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ድረስ ሱዳን ያጋጠሚትን ችግሮች በሰላም እንድትፈታ ጉልህ ሚና መጫወታቸውን አስታውሰዋል። ዛሬም ሱዳን ያጋጠማት የሰላም መደፍረስ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ኢትዮጵያ የነበራትን ታሪካዊ ሚና ለመወጣት ሙሉ ፍላጎት እና ዝግጁነት እንዳላት አረጋግጠዋል። ኢትዮጵያ ሱዳናውያን ያለ ምንም የውጭ አካል ጣልቃ ገብነት ችግሮቻቸውን በራሳቸው ጥበብና ዕውቀት ይፈታሉ ብላ እንደምታምን ነው የተናገሩት።

ሚኒስቴሩ በሱዳን ወቅታዊ የፀጥታ መደፍረስን ተከትሎ በዋናው መስሪያ ቤት እና ካርቱም በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ አማካኝነት በአገሪቷ የሚገኙ ዜጎቻችንን ደህንነት ለማስጠበቅ በቅርበት እየተከታተለ ነው ብለዋል፡፡

ለዚህም የተለያዩ መስሪያ ቤቶችንና አጎራባች ክልሎችን በአባልነት ያቀፈ ግብረ-ኃይል በአገር አቀፍ ደረጃ መቋቋሙን መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# ለውጭ ገበያ ከቀረበ የሥጋና የእርድ ተረፈ ምርት 74 ሚሊዮን ዶላር ተገኘ

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ ካቀረበችው የሥጋና የእርድ ተረፈ ምርቶች 74 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢንስቲትዩቱ የማህበራዊ ምጣኔ ሀብት አስተዳደር ምርምር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሳህሉ ሙሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የሥጋና የእርድ ተረፈ ምርቶች በኢንዱስትሪ ውስጥ ተቀነባብረው በስፋት ለውጭ ገበያ ተልከዋል።

ለውጭ ገበያ ከቀረበው 16 ሺህ 300 ቶን የሥጋና የእርድ ተረፈ ምርት 74 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ተችሏል ሲሉ አስረድተዋል። በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከበግና የፍየል ሥጋ 8 ሺህ 600 ቶን ወደ ውጭ ገበያ በመላክ 63 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን አስታውቀዋል። በአንጻሩ ለውጭ ገበያ ከቀረበው 3 ሺህ 400 ቶን የእርድ ተረፈ ምርት ዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል ብለዋል፡፡

ከዓሣ ሥጋ፣ ከተቀነባበረ ማርና ሰም፣ ወተትና የወተት ተዋፅኦ፣ ከዶሮ፣ መኖ ምርቶች ደግሞ ከሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል ሲሉ አስረድተዋል። በአሁኑ ወቅት የምግብ ደህንነትና ጥራት መስፈርቶችን ያሟሉ 12 የሥጋ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እያቀረቡ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ሳህሉ ገለጻ፤ ኢንስቲትዩቱ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን የምርት መጠንና የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ አቅዶ እየሠራ ይገኛል። ምርቶች ወደ ተለያዩ የውጭ አገራት በመላክ ላይ መሆናቸውን የገለጹት ዶክተር ሳህሉ፤ የሥጋ ምርቶች ወደተባበሩት አረብ ኢሚሬትስና ሳውዲ አረቢያ በስፋት እንደሚላክ አስታውቀዋል። በተጨማሪ የስጋ ምርት ወደኳታር፣ ኦማንና ሌሎች የገልፍ አገራት ላይ በመቅረብ ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

የእርድ ተረፈ ምርቶች ደግሞ ወደ እስያ አገራትና ምዕራብ አፍሪካ አገራት የሚላክ መሆኑን ጠቅሰው፤ ማርና የሰም ምርት ደግሞ ወደ አውሮፓ አገራት ይላካል ብለዋል፡፡

የኢንዱስትሪዎችን ግብዓቶች ፍላጎት በማሟላት ረገድ ከአርብቶ አደሩ ጀምሮ የስጋና እንስሳት ተዋጽኦዎች ምርት ልማት ሥራዎች መሠራታቸውን የገለጹት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ግብዓቶቹን የማሳደግ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

የእርድ እንስሳት፤ ወተት፣ ማርና ሰም፣ የዓሣ ስጋ ግብዓቶችን በማቅረብ ተቀነባብረው ገበያው በሚፈልገው ጥራትና መጠን መላክ የሚያስችል ሥራዎች መከናወኑን ገልጸው ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያና የእንስሳት ውጤቶችን በኢንዱስትሪ ለማቀነባበር የሚደረጉ ጥረቶችን በመደገፍ ላይ መሆኑን ምክትል ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

አገሪቱ ካላት የእንስሳት ሀብት አንጻር ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ማግኘት ትችላለች። ኢንስቲትዩቱም የአገሪቷን የእንስሳት ሀብት አቅም ከግምት ውስጥ ያስገባ ተጨማሪ ሥራ ለማከናወን ትኩረት አድርጎ እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ ለሰላሟ የሰሩትን ሁሉ አብዝታ ታመሰግናለች!

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ ለሰላም ትልቅ ትርጉም የምንሰጥ ሕዝቦች ነን። መንፈሳዊ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ እሴቶቻችን ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጡና አብዝተው የሚሰብኩ ናቸው። የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችንም ለሰላም ትኩረት የሚሰጥ፣ የሚዘክርና አብዝቶ ለሰላም ጥበቃ የሚያደርግ ነው።

"እያ እከሌ "በሰላም አደርክ፤ ቀዬው አገሩ ሰላም አድሯል ከሚለው የተለመደው የማለዳ ሰላምታ ጀምሮ፤ ቀኑን ሙሉ ባለው ማኅበራዊ መስተጋብራችን ጎልቶ የሚደመጠው ሰላም የሚለው ቃል፣ እንደ ሕዝብ ስለ ሰላም ያለንን ቀናኢነት አመላካች ነው።

ችግሮቻችንን በራሳችን ዘመናት በተሻገሩ የዳበሩ የሰላም እሴቶች በመፍታት፤ ሁሌም ለሰላም ያለንን ቁርጠኝነት በተጨባጭ የምናሳይና በዚህም ከፍያለ የስነ ልቦና ከፍታና መንፈሳዊ ልእልና ያለን ሕዝቦች ነን።

የህይወት መስዋእትነት በሚጠይቁ ዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች ወስጥ በመሳተፍ፤ ለሰላም ያለንን ቁርጠኝነት በተግባር አስመስክረን ዓለም አቀፍ እውቅና አትርፈናል። በመሪም ደረጃ ዓለም አቀፉን የሰላም ኖቤል ተሸላሚ በመሆን ዓለም ስለ ሰላም ያለንን አቋምና ትክክለኛ መረዳት በተጨባጭ እንዲረዳ አድርገናል።

ይህም ሆኖ ግን በየወቅቱ በሚፈጠሩ አለመግባባቶች ሰላማችን እየተረበሸ ግጭት ውስጥ መግባታችን፤ እንደ አገር አላስፈላጊ ዋጋ መክፈላችን፤ በዚህም በብዙ የልብ ስብራት ውስጥ የማለፋችን እውነታ ዛሬ ድረስ ያልተሻገርነው ትልቁ ተግዳሮታችን ሆኗል።

በቅርቡ በሰሜኑ የአገሪቱ አካባቢዎች የተካሄደው ጦርነት የዚሁ እውነታ አንዱ መገለጫ ነው። በወቅቱ የተፈጠረውን ችግር በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ በውይይት ልንፈታ የምንችልበት ሰፊ ዕድል የነበረን ቢሆንም፤ ይህንን ዕድል መጠቀም ባለመቻላችን አስከፊ ወደ ሆነ ጦርነት ለመግባት ተገደናል።

መላው ሕዝባችንም አልፈን ከመጣናቸውና የግጭትና የጦርነት ታሪኮቻችን ካስከፈሉን ከፍያለ ዋጋ አንጻር፤ ጦርነትን በየትኛውም መልኩ አምርሮ የሚቃወም፤ ጦርነት ትርፍ የሌለበት የጥፋት ድግስ መሆኑን በአግባቡ የሚረዳ ቢሆንም፤ ተፈጥሮ የነበረው ችግር የአገርን ህልውና ስጋት ውስጥ በመጨመሩ ተገድዶ በጦርነቱ ተሳታፊ ሆኗል።

በጦርነቱ ወቅትም በሕዝብ ይሁንታ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በአንድ እጁ ብረት በሌላ እጁ የሰላም ሰንደቅ በማውለብለብ፤ ሕዝባችን እንደ ሕዝብ ስለሰላም ያለውን ከበሬታ በተጨባጭ አሳይቷል። በዚህም የሚጨበጥ ፍሬ ማፍራት ችሏል።

በወቅቱም የሕዝባችን የሰላም መሻት ፍሬ እንዲያፈራ ሕወሓትን ጨምሮ በአፍሪካ ኅብረት እና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በኩል የታየው ቀና ተሳትፎ፤ በብዙ መልኩ የሚበረታታ እና እውቅና ሊሰጠው የሚገባ እንደሆነ ይታመናል።

በተለይም የአፍሪካ ኅብረት "ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ "የሚለውን የአህጉሪቱ ሕዝቦች የራስን ችግር ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት የመፍታት መነቃቃት እውን በማድረግ ለችግሩ መፍትሄ ለማፈላለግ የሄደበት መንገድ በቀጣይ በአህጉሪቱ ተመሳሳይ ችግሮች ቢያጋጥሙ ለመፍታት የሚያስችል ስኬታማ ተሞክሮ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብም፣ በአንድም ይሁን በሌላ ለችግሩ ትኩረት በመስጠት፤ በመንግስት በኩል ለተጀመረው የሰላም ጥረት ተጨማሪ አቅም በመሆን ችግሩ በሰላማዊ ድርድር በሰላም ስምምነት እንዲቋጭ ያደረገው ድጋፍ ምስጋና ሊቸረው የሚገባ ነው።

ምንም እንኳን የራሳቸው የቤታቸውና የአገራቸው ጉዳይ ቢሆንም በአገር ውስጥ ያሉ ታዋቂ ሰዎች ራሳቸውን የመፍትሄ አካል በማድረግ የሄዱበት ርቀት የሚበረታታ ነው። ይህ በአገራችን የቀደመ ታሪክ ብዙም ያልተለመደው አዲስ ተሞክሮ በቀጣይ አንድ የችግር መፍቻ አቅም ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባውም ነው።

በአጠቃላይ የሕዝባችን የሁሌ መሻት የሆነውን አገራዊ ሰላም በማስፈን ሂደት ውስጥ በአንድም ይሁን በሌላ ተሳትፎ ያደረጋችሁ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ተቋማት፣ አገራት እና የአገራት መሪዎች እንዲሁም ታዋቂ ግለሰቦች ኢትዮጵያ ከፍ ያለ ምስጋናዋን ታቀርብላችኋለች። ይህ አስተዋጿችሁ በአገራችን ሰላም ግንባታም ሆነ በታሪካችን ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚይዝ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ሠላምን ለመለሱ ክብርና ምስጋና

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

‹‹ሰላም›› ይሉት ቃል በሶስት ፊደላት ተወስኖ፣ በአጭር አባባል የተገለጠ ሀሳብ ነው። የቃሉ ምጣኔ ያነሰ፣ የተመጠነ ይምሰል እንጂ የትርጓሜው ሀያልነት ዓለምን ሁሉ ይገዛል። ታሪክን ይቀይራል። ለዚህም ነው ስለሰላም ከልብ የጣሩ፣ ቃሉን አድምቀው የጻፉ፣ መኖሩን አብዝተው የሻቱ ሁሉ ከስረው የማያውቁት ።

የከሳቴ ብርሀን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ስለሰላም ምንነት እንዲህ ሲል ፍቺውን አስፍሯል። ‹‹ሰላም ማለት የፍቅር ፍሬ ነገር ፣ ያማረ፣ የተወደደ ፣ የቀና ነገር ፤ ፍቅር አንድነት ፣ መስማማት፣ በሀሳብ በስራ መግባባት ያለበት ፣ ይሄ የእኔ ነው የአንተ አይደለም እየተባባሉ አለመቀናናት፣ እንደ አንድ ነፍስ እንደ አንድ ስጋ መሆን ማለት ነው››

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ምርምር ማዕከል ባሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላትም ስለሰላም ምንነት እንዲህ ሲል አስፍሯል። ‹‹ሰላም ረብሻ፣ ሁከት ፣ ጦርነት የሌለበት የተረጋጋ፣ ሁኔታ ደህንነት፣ ጤንነት፣ የአዕምሮ እርፍት ማለት ነው።

ይህ ታላቅ የዓለማችን ድንቅ ስጦታ በምድር ላሉ ፍጥረታት ሁሉ የውሀና የእስትንፋስ ያክል አስፈላጊ የሚባል ነው። ያለ ሰላም ህይወትና ኑሮ፣ ትምህርትና ትዳር አይታሰብም። ያለሰላም በሰላም መኖር፣ ተኝቶ መነሳት፣ ርቆ መራመድ አይታቀድም።

መቼም ቢሆን የሰላም ዋጋ በገንዘብ የሚተመን፣ በሚዛን የሚለካ አይደለም። ሰላም ሁሌም ዘብ ይቆምለታል፣ ውሎ አዳሩን የሚያከብር፣ ባህር ሞገዱን የሚሻገር ዕልፍ ወታደር ይሾምለታል። የሀይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ ሽማግሌዎች፣ የአገር መሪዎች በየጊዜው ስሙን አንስተው፣ ያወሱታል።

የሰላም እጦት ከቤት ከቀዬ ያፈናቅላል፣ ከእናት አገር ምድር ያሰድዳል፣ ክቡር ህይወትን ነጥቆ ሀብት ጥሪትን ያሳጣል። አገራችን ለዓመታት ያለፈችባቸው የጦርነት ታሪኮች ሰላምን አጥብቃ እንድትሻ ሲያስገድዳት ቆይቷል። ይህ አይነቱ አስከፊ ጠባሳ ያሳደረው ተጽዕኖም በታሰበው ልክ በዕድገት ጎዳና እንዳትራመድ ጋሬጣ ሆኖባት ዘልቋል። በጦርነት ውስጥ እንደ ጸሀይ ብልጭ የማትል ሰላም በታጣች ጊዜ የኑሮ፣ የህይወት ደርዝ ይናዳል፡ የዕንቅልፍ ወጉ የመኖር እፎይታው ይናፈቃል።

በአብዛኞቹ የአፍሪካ አገራት በተካሄዱ የእርስበርስ ግጭቶች ለቁጥር የሚያታክት የሰው ልጆች ህይወት መስዋዕት ሆኗል። በቀላሉ ሊተኩ የማይችል ሀብት ንብረት ወድሟል። በሺዎቹ የሚቆጠሩ ህዝቦች ለመፈናቀልና ስደት ተዳርገዋል። በነዚህ አገራት አሁንም ድረስ ያልተገኘው ሰላም ድህነትን አባብሶ አገር እስከማፍረስ ደርሷል።

በአገረ ሶርያ፣ የመን፣ አፍጋንስቲን፣ ሊቢያና ሶማልያ የተከሰተው እረፍት አልባ ጦርነት በርካታ ዋጋ እያስከፈለ ነው። አሁንም ድረስ የንጹሀን ህይወት ይጠፋል፣ ንብረት ይወድማል፣ ከተማ በአየርና በምድር ጥቃት ይደበደባል። በየዕለቱ አገር በሚናድ፣ በሚፈርስበት አጋጣሚ ሁሉ ህይወት ያለተስፋ መቀጠሉ እውነት ሆኗል።

የዚህ ስፍራ ነፍሶች የየዕለት ስንቃቸው ሞትና ስቃይ ነው። ስለነገ የሚተርፍ ጭላንጭል ህልምና ዕቅድ የላቸውም። እስከ ህቅታቸው ሊያዘልቃቸው የሚችል የሰላም ርጋፊ ከእጃቸው አይገኝም፤ ዘወትር የተማሰ መቃብራቸውን ያስባሉ፣ የጽልመት ኑሯቸው በመከራ የተለወሰ፣ በመሳቀቅ የተመላ ነው። የእነሱ የሰቆቃ ዓለም መቼም በርቶ አያውቅም። በድቅድቅ ጨለማ እንደተዋጠ ነገን በጭንቅ ያሻግራቸዋል።

ሰላምን አጥብቀው የሚሹ ኃይሎች ጥቂት የመሆን እውነት ጦርነት እንዲቀጥል፣ ድህነት እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኗል። ዛሬ በነዚህ ስፍራዎች ነጭዋ እርግብ ክንፏን ዘርግታ አትበርም፣ የሰላም አየር ይሉት ጉዳይ ዘበት ነው። ከሰው ልጆች ዘንድ ህይወትና ኑሮ የሚባል ዓለም ፈጽሞ ታሪክ ሆኗል።

ሰላም በብዙ እውነታዎች ይፈተናል። በእርስ በርስ ጦርነት፣ በድንበር ይገባኛል ግጭት፣ በጎሳና ብሄር የእኔ እበልጥ ስሜት፣ ስልጣን በመንጠቅ ሽሚያና በሌሎችም። ሁልግዜም የዚህ አይነቱ የሰላ ሰይፍ በራሱ ጽንፍ ብቻ አይቆምም። የመድረሻው አንዱ ጫፍ ሌላውን ወገን አጥቅቶ በክፉ ታሪክ ይገለጣል። በግጭቱ የሌሉበትን ንጹሀን አጥቅቶ ክፉ አሻራውን ያትማል።

አገራችን ኢትዮጵያ ባሳለፈችው የጦርነትና የፖለቲካ ግጭት በቀላሉ የማትተካቸውን ሰብአዊ እሴቶች እንደዋዛ ተነጥቃለች። ከሰላም ይልቅ ነፍጥ ማንሳትን በወደዱ ኃይሎች የደረሰው ውድመትም የድህነት ታሪኳን አድምቆ ለውጭ ኃይሎች ፍላጎት ጭምር ሲያጋልጣት ቆይቷል።

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተካሄደው አስከፊ ጦርነት ከምንም በላይ አይተኬውን የሰውልጆች ሕይወት ተነጥቋል። አገር መልማት፣ ማደግ፣ መለወጥ በሚገባት ዘመን እንደቀልድ ዕድሜና ሀብት ባክኗል። የወገን እሴት፣ ዕውቀትና ተስፋው በጦርነት እሳት ነዶ ሀዘን መከራን አሳጭዷል።

ይህ ሁሉ የሆነው በግጭቱ መሀል ጦርነቱን የረታ ክፋትን ያሸነፈ የሰላም ሙከራ አለመኖሩ ነው። በእሳት ዙሪያ ከበው ግጭት የሚያቀጣጥሉ፣ ንዳድ ቃጠሎውን የሚሞቁ ኃይሎችም እስከዛሬ ቤንዜን ከመጨመር የዘለለ መፍትሄን አላመጡም።

በውጭ አገራት የሚገኙ አንዳንድ ዲያስፖራ ነን ባዮች ወሬና አሉልባታን መተዳደሪያ አድርገው ሰላምን ሲያርቁ፣ እፎይታን ሲነጥቁ ቆይተዋል። እነዚህ ኃይሎች በየቀኑ ለሚሞተውና ለሚፈናቀለው ወገን አንዳች መላን አልፈየዱም። በተቃራኒው ክፉ መረጃን እየነዙ፣ ህዝብን ከህዝብ፣ ታሪክን ከታሪክ ሲያላትሙ ኖረዋል።

ይህ ብቻ አይደለም ለጦርነቱ መጀመርና መባባስ በምክንያትነት የሚጠቀሱ በርካታ የማህበራዊ ገጾች ሰላምን አርቀው፣ እሳትን በማንደዱ በኩል የላቀ አስተዋጽኦ ነበራቸው። የእነሱን ስሜት ተከትሎ ጣልቃ እንግባ ባዮቹ ምዕራባውን ውሻ በቀደደው ጅብ ሆነው ለመግባት ሲሯሯጡ መኖራቸውን ትውልድ አይዘነጋውም።

በነዚህ የታሪክ ስብራቶች መሀል ግን መልካምነትን የተላበሱ፣ ሰላምን ሽተው ጦርነትን የተጸየፉ ወገኖች አልታጡም። ስለሰላም ርቀው የተጓዙበት ጎዳና ሁሌ አልጋ በአልጋ ባይሆንም፣ እነዚያን ክፉ ቀናት ለማሻገር ስለሰላም ዘምረው ነጭ ርግብ ለመልቀቅ ቦዝነው አያውቁም።

እርግጥ ነው በወቅቱ ተስፋቸውን የሚነጥቅ፣ እርግባቸውን የሚያጠምድ ክፉ ድመት አላጡም። መንገዳቸውን የሚያደናቅፍ የብረት ወጥመድም ከእግራቸው ስር ነበር። እነሱ ግን እሳቱን አልፈው፣ ባህሩን ተሻግረው ‹‹እርቅ ይውረድ፣ ሰላም ይስፈን›› ብለዋል። ኩርፊያን አስወግደው፣ ጠብን አርቀው የጨለማ ብርሀን ሊሆኑ ታግለዋል።

በአገራችን በመልካም ማንነታቸው ሥብዕናቸው የተገነባ ታዋቂ ሰዎች፣ እናቶች ስለሰላም ጎንበስ ብለው ተማጽነዋል። ያለአገር ሰላም ክብርና ዝና አለመኖሩ ቢገባቸው ተንበርክከው ለምነዋል። ይህ እውነታ ሁሌም ስማቸውን ከስም በላይ እንዳደመቀው ይቀጥላል።

‹‹የአፍሪካውያንን ችግር በአፍሪካውያን›› ያሉ የክፉ ቀን ወገኖች በርካቶች የእሳት ላይ ቤንዚን በሆኑበት ዘመን የነደደውን ሊያጠፉ ቀዝቃዛ ውሀ ይዘው ቀርበዋል። መልካሞቹ አፍሪካዊያን ወንድሞቻችን ስለሰላም ሌት ተጉዘዋል።

እነሆ ለዓመታት የተጉበት፣ ድካማቸው ፍሬ ይዞ ውጤት አፍርቷል። የትናንቱ ጦርነት በሰላም ስምምነት ድል ተነስቶ ደም መፋሰስ ቆሟል። የጥይት ድምጽ እንዳይኖር፣ ፍጹም የሰላም እንዲሰፍን ያደረጉት ጥረትም ተሳክቷል። ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ ከቆየችበት የሰላም ርሀብ አገግማ ወደ ትናንት ማንነቷ ልትመለስ ጉዞ ጀምራለች።

ይህች የታሪክና የነጻነት አገር ስለሰላም ሲሉ ከጎኗ የቆሙትን የክፉ ቀን ደጎች ፈጽሞ አትዘነጋም። ዛሬ በተራዋ እውቅና ልትሰጣቸው ከልብ ልታመሰግናቸው ቀን ቆርጣ ወስናለች። ስለሰላም፣ የሰላም አርማን ያነገቡ፣ ጦርነትን ታግለው ላሸነፉ ሁሉ ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን ›› ስትል በምስጋና እጅ ትነሳለች።

ዜና




# የኦሮሚያ ክልል ለአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር 12ሺህ ኩንታል የችግኝ ዘር አሰራጭቷል

## -አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ ተዘጋጅቷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልል ለአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከ12ሺህ ኩንታል በላይ የችግኝ ዘር ለተለያዩ የችግኝ ጣቢያዎች ማሰራጨቱን አስታወቀ።በአሁኑ ወቅትም አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ መዘጋጀቱ ተጠቅሷል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ ሥራው በዋናነት አርሶ አደሩ የተፋሰስ ልማት ላይ ትኩረት አድርጎ እየተሠራ ይገኛል።ከ12ሺህ ኩንታል በላይ የችግኝ ዘር በእያንዳንዱ የችግኝ ጣቢያ ላይ ተከፋፍሎ በአሁኑ ወቅት ወደ አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ ተዘጋጅቷል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ በበጋው ስድስት ሺህ የሚሆኑ የተፋሰስ ልማቶች ተለይተዋል።ከዚህ ውስጥ አንድ ሚሊዮን 30 ሺህ የሚሆነው መሬት ላይ የተፋሰስ ልማት «ስትራክቸሮች» ተሠርተዋል።ውሃን ሊይዙ የሚችሉ እንዲሁም ውሃን ለማውጣት አመቺ በሆነ መልኩ በዝግጅት ምዕራፉ ወቅት ሲሠራ ነው የቆየው።በዚህም ወደ ስድስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ተሳትፎ አድርጎበታል።

የችግኝ ተከላውን ከወዲሁ ለመጀመር ችግኝ የማዘጋጀት ሥራው በስፋት መጀመሩን የቢሮ ኃላፊው አስታውቀዋል።በአርሶ አደሩ ችግኝ የሚተከልባቸው ቦታዎች እና በስፋት ችግኝ ጣቢያዎች ላይ ችግኝ እንዲዘጋጅ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።በዚህም ከ12ሺህ ኩንታል በላይ የችግኝ ዘር ለችግኝ ጣቢያዎች ተከፋፍሎ በአሁኑ ወቅት ወደ አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ ተዘጋጅቷል።ቀሪውም ሙሉ ለሙሉ በቅርቡ ዝግጁ ይሆናሉ ነው ያሉት፡፡

ዘንድሮ ከሌሎች ዓመታት በተለየ ሁኔታ እየተሠራ እንዳለ የገለጹት ቢሮ ኃላፊው፤ የደን ችግኝን ብቻ ሳይሆን ለአፈር ጥበቃው የሚያገለግሉና ለምግብነት የሚሆኑ ተክሎች ላይ ትኩረት መሰጠቱንም ተናግረዋል።

እንደ አቦካዶ፣ ማንጎ፣ ብርቱካንና የመሳሰሉትን ተክሎች ከዚህ ቀደም ባልተለመዱ አካባቢዎች ላይ ለመትከል በየችግኝ ጣቢያዎች ሰፊ ዝግጅት ተደርጓልም ነው ያሉት።

«ከዚህ ቀደም የነበረው የደን መጠን እየተመናመነ ነበር።ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ ድርቅ አርሶ አደሮች ላይ ጉዳት ሲያስከትል ቆይቷል።ሆኖም በአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብሩ በየቦታው ጠፍተው የነበሩት የውሃ ምንጮች በሰፊው መመለስ አስችሏል» ሲሉ ገልጸዋል።

የአረንጓዴ አሻራ ልማቱ ይህንና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው የገለጹት ኃላፊው፤ ምርታማነትን ለመጨመር እንዲሁም የአግሮ ኢኮሎጂውን በመጠበቅ ለአርሶ አደሩ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጥ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

በዘንድሮ ዓመት በክልሉ በጠቅላላው አራት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ችግኝ ለመትከልም ታቅዶ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

# ክልሉ ከአራት ቢሊዮን ብር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የአፋር ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይዘሮ አይሻ መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሁለት እና ሦስት ዓመታት በሰሜን ኢትዮጵያ ከነበረው ጦርነት ጋራ ተያይዞ የክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ተዳክሞ ቆይቷል።

በአሁኑ ጊዜ በክልሉ ሰላም በመስፈኑ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴው መነቃቃቱን ጠቁመው፤ ባለፉት ስምንት ወራትም ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል ብለዋል።

ለሁሉም ነገር ሰላም ወሳኝ ነው ያሉት ወይዘሮ አይሻ፤ የውጭም ይሁን የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ተረጋግተው የኢንቨስትመንት ሥራቸውን እንዲሠሩ ዘላቂ ሰላምን ማስፈን እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ሰላም ከተፈጠረ በኋላ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የውጭ እና የአገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ወደ ክልሉ እየመጡ መሆኑን አመልክተው፤ በዚህም ባለፉት ስምንት ወራት 97 ኢንቨስተሮች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ወስደው ወደ ሥራ መግባታቸውን ገልጸዋል፡፡

የኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች አራት ቢሊዮን 323 ሚሊዮን 025 ሺ 606 ብር ያስመዘገቡ መሆኑን ገልጸው፤ እነዚህ ኢንቨስትመንቶችም ለ6ሺ 100 ወጣቶች ቋሚ እና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩም አመልክተዋል፡፡

በክልሉ ኢንቨስት ለማድረግ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰዱ ባለሀብቶች በአብዛኛው ግብርና ላይ ለመሰማራት መሆኑን ጠቁመው፤ በዘንድሮው በጀት ዓመት ስምንት ወራት ውስጥ የኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰጣቸው 52 በግብርና፣12 በኢንዱስትሪ፣ 20 በኮንስትራክሽን፣ 5 በእንስሳት እርባታ፣ 5 በሆቴል ዘርፍ፣ አንድ ማዕድን ላይ እንዲሁም 2 በማሽነሪዎች ኪራይ ላይ እንደሚሰማሩ ኮሚሽነሯ አብራርተዋል፡፡

ከዚህ በፊት ፍቃድ ወስደው ወደ ሥራ ያልገቡና ወደ ሥራ የገቡ ባለሀብቶችን በመለየት የክትትል ሥራ መከናወኑን ጠቁመው፤ ወደ ሥራ የገቡትን ጠንክረው እንዲሠሩ ማበረታታት፣ ሥራ ያልጀመሩትም በፍጥነት ሥራ እንዲጀምሩ አቅጣጫ በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉን ተናግረዋል።

ክትትል እና ድጋፍ ተደርጎላቸው መሬት አጥረው አስቀምጠው ወደ ሥራ ያልገቡትን ፍቃዳቸውን ለመሰረዝ በዝግጅት ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የአፋር ክልል በተፈጥሮ ሀብት የታደለ እንደሆነ ያስታወሱት ወይዘሮ አይሻ በቱሪዝም፣ በሰፋፊ የእርሻ መሬቶች እና በእንስሳት ሀብት ልማት ለኢንቨስትመንት ምቹ መሆኑን ተናግረዋል።

በክልሉ ኢንቨስተሮች በፈለጉት ዘርፍ ቢሰማሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ ጠቁመው፤ ይህን ዕድል ለመጠቀም የውጭ እና የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ መጥተው እንዲያለሙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# «ጀኔራል ሰዓረ ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ላይ እንደገለጹት፣ በአገሪቱ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ አንዳንድ ፅኩይ ኃይሎች በፈጠሩት ሴራ ጥቁር ታሪክ አስቀምጠዋል። ነገር ግን የጀኔራሉ ሐውልት መገንባት ትውልዱ ጀግኖችን እየዘከረ የሚያልፍበትን ዕድል ይፈጥራል።

ጀግኖችን የሚያሳጡና አገርን የሚጎዱ የታሪክ ምዕራፎች እንዳይደገሙ ትምህርት ወስደን በቀጣይ በትኩረት ልንሠራ ይገባል በማለትም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። በተለይም ሆደ ሰፊነትን በመላበስ በይቅርታና በፍትሕ በመሻገር የተሻለ ነገን መገንባት እንደሚገባም ነው ሚኒስትሩ የተናገሩት።

የጀኔራሉ ባለቤት ኮሎኔል ፅጌ አለማየሁ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለጀኔራል ሰዓረ ጀግንነቱን የሚመጥን ሐውልት በስሙ ስላቆመለት አመስግነዋል።

እንደ ኢዜአ ዘገባ፤ መታሰቢያ ፓርክና ሐውልቱ በአዲስ አበባ ቦሌ ሩዋንዳ አካባቢ በስማቸው በተሰየመ ፓርክ ውስጥ ክብራቸውን በሚመጥን መልኩ ተገንብቶ ለምርቃት መብቃቱ ተገልጿል።

የጀኔራል ሰዓረ መኮንን የመታሰቢያ ሐውልት እና ፓርክ፤ ከሃሳቡ ጀምሮ ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ ያሠራው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሆኑ ታውቋል።የቀድሞ የኢፌዴሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጀኔራል ሰዓረ መኮንን አገር ወዳድ የኢትዮጵያ ልጅ እንደነበሩ ተወስቷል።

ጀኔራል ሰዓረ ከግንቦት 2010 ዓ.ም ሕይወታቸው እስካለፈበት ሰኔ 15/2011 ዓ.ም ድረስ የኢፌዴሪ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም በመሆን ኢትዮጵያን በታላቅ ታማኝነትና ቅንነት አገልግለዋል።

# ለኩላሊት ሕክምና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በመሆኑ በሕክምና ባለሙያዎቹ ዘንድ ጥርጣሬ በመፍጠሩ የተነሳ ሕክምናውን ማግኘት እንደማይችል ተነግሮት ከልመና ካገኘው 16 ሺ ዶላር 5ሺ ዶላሩ ብቻ ተመላሽ ተደርጎለት ሕክምናውን ሳያገኝ ወደ አገሩ መመለሱን ገልጿል።

ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ አገር ለሕክምና በሚሄዱበት ጊዜም ለመብታቸው መከበር የሚከራከርና ገንዘባቸውን የሚያስመልስ አካል ባለመኖሩም በርካቶች ለእንደእኔ ዓይነት እንግልት ይጋለጣሉ ሲል አቶ ሁሴን ያነሳል፡፡

አቶ ሁሴን በድጋሚ ሕክምናውን ለማግኘት ጎዳና ላይ መለመን ግድ ይለው ነበርና ገንዘቡን አሰባስቦ ወደ ሕንድ በመሄድ የተሳካ ሕክምና አግኝቶ መመለሱን ነግሮናል፡፡

አቶ ሁሴን በርካቶች የኩላሊት ሥራ ማቆም ሲያጋጥም ፈተናው ንቅለ ተከላ እስከ ማድረግ ቢመስላቸውም የሕክምና ክትትሉና የሚወሰደው መድኃኒት የዕድሜ ልክ መሆኑን ይገልጻል፡፡

በኢትዮጵያ ለኩላሊት ህመምተኞች የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ በመሆኑም ህመምተኞች ሕክምናውን አገር ውስጥ ካለማግኘታቸው በተጨማሪም የመድኃኒት መጥፋት ዋነኛው ችግር እንደሆነባቸው ይገልጻል፡፡

ስሟን መግለጽ ያልፈለገች ወጣትም የኩላሊት ህመምተኞች መድኃኒት የሚወስዱት የዕድሜ ልክ እንደመሆኑና የመድኃኒቱ አቅርቦት እጥረት በመኖሩ እስከመዋዋስ እንደሚደርሱ ትናገራለች፡፡

ለመድኃኒት በወር ከ6 ሺ ብር በላይ አወጣለሁ የምትለው ወጣት፤ ከዚህ በተጨማሪም በየጊዜው የምናደርጋቸው ምርመራዎች በመንግሥት ሆስፒታሎች ስለማይገኙ በግል ሆስፒታል ለከፍተኛ ወጪ እየተዳረግን ነው ትላለች፡፡

በጤና ሚኒስቴር የግብአት ክፍል ኃላፊ አቶ ረጋሳ ባይሳ በበኩላቸው፤ በኩላሊት ሕምመተኞች ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶት ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ጭምር እየተሠራ ነው ብለዋል።የመድኃኒት እጥረትን ለመቅረፍም በአንድ የጤና ተቋም የጠፋ መድኃኒት በሌላ የጤና ተቋም ማግኘት ይቻላል ነው ያሉት።

በአሁኑ ጊዜም በጦርነት ሙሉ በሙሉ ሥራ ያቆሙ ሆስፒታሎች በመኖራቸው እነሱን ሥራ ለማስጀመር በትኩረት እየተሠራ ቢሆንም በቀጣይ የኩላሊት ህመምተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ሆስፒታሎች ጉዳይ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል ብለዋል።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "ኢትዮጵያ ታመሰግናለች!"

**የመደላድል ወግ፤**

ከአገራዊ ብሂሎቻችን መካከል "ሰማይ ተቀደደ ቢሉት፤ ሽማግሌ ይሰፋዋል አለ ይባላል" የሚለው አገላለጽ በርግጥም የሰማይን ወርድና ርዝመት ያህል የገዘፈ መልእክት አምቆ እንደያዘ መረዳት ይቻላል። ዋናው የመልእክቱ ጭብጥ በሽምግልናና በንግግር የማይፈታ ችግርና ቅራኔ እንደሌለ ለማሳየት ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የከበሩ የባህልና የትውፊት ፀጋ በታደሉ አገራት ዘንድ ለሽምግልና የሚሰጠው ክብር እጅግ የላቀ ነው። "ሽማግሌ ሲጠፋ የአገር ፊት በማዲያት ይጠቁራል" የሚባለውም ስለዚሁ ሳይሆን አይቀርም።

ሽማግሌዎች በተያዙት የእርቅ ሂደት ተው ሲባል ያልተወ፣ ይቅር ተባባሉ ሲባል ልቡን ያደነደነና በእምቢታው የጸና ግለሰብም ሆነ ቡድን ማሕበረሰቡ በአሜንታ ከተቀበለው ሥርዓት፣ ወግና ባህል ጋር የመጋጨት ያህል ስለሚታመንበት እንደ ቀድሞው በለመደው አኗኗር ልቀጥል ቢል በእጅጉ መቸገሩ አይቀርም። በይቅርታ የመቀባበልን ብርታት ለመግለጽ ሲፈለግም "ይቅር ለእግዜር ወድቆ አይሰበር፤ ሞቶ አይቀበር" እየተባለም ይሞካሻል።

"ልቡ ለቂም፣ ቃሉ ለበደል፣ እጁ ለመግደል" የጨከነና የበረታ ሰው እንኳን ቢሆን የአበው/እመው የማሸማገል እውቀትና ጥበብ ደንዳና ልብን ለመስበር፣ መራራ ቋንቋን ለማለዘብና ደም የነካ እጅንም ሳይቀር የመፈወስ አቅሙ ከፍ ያለ ነው። ስለዚህም ነው "እርቅ ደም ያደርቅ" እየተባለ በምሳሌ የሚነገረው።

ሰሞኑን በተከታታይ ያከበርናቸው የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት በዋነኛነት ያስተላለፉልን ታላቅ የጋራ መልእክት በእርቅ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነበር። የእርቁ ማእከላዊ ጭብጥ ደግሞ ሰው ከራሱ፣ ሰው ከፈጣሪው፣ ሰው ከሰውና ሰው ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ መኖር እንዲችል የሚያበረታታና የሚያስተምር ነው።

ይቅርታ ማድረግን አስመልክቶ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግሞ የሚጠቀስ አንድ አስደናቂ ታሪክ ተመዝግቧል። "ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፤ ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን? አለው። ኢየሱስም መልሶ ‹እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም። " ብሎ መለሰለት" (ማቴዎስ 18)።

እለት በእለት ለሚያጋጥሙን በርካታ እርቅ ተኮር ጉዳዮች ከዚህ ታሪክ ብዙ ቁምነገሮችን መቅሰም ይቻላል። መበደልም ሆነ ይቅር መባባል "እንደ መስቀል ወፍ" በሕይወታችን ውስጥ ዓመት እየጠበቀ አንድ ጊዜ የሚከሰት አጋጣሚ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው በተለያዩ ምክንያቶችና ጉዳዮች ሳይግባባ ቀርቶ ሊጋጭ ወይንም ሊገጨት፣ ሊበድል ወይንም ሊበድሉት፣ ሌሎችን ሊያሳዝን ወይም እርሱ ራሱ ሰዎችን ሊያሳዝን መቻሉ ከተፈጥሯዊ ማንነታችን ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው።

ከራስ ጓዳ እስከ ሕዝብ አደባባይ፣ ከቤተሰብ እስከ ማሕበረሰብ፣ ከትዳር እስከ አገር መጋጨት፣ መኳረፍና ይቅር መባባል በቁጥርም ሆነ በዓይነት ተወስኖ የሚጠናቀቅ የአንድ ሰሞን ጉዳይ ብቻ አይደለም። ስለዚህም ሳይሆን አይቀርም ጴጥሮስ የራሱ ግምት በመስጠት ይቅርታን በሰባት ጊዜ ብቻ መወሰኑ ትክክል ያለመሆኑን ኢየሱስ የነገረውና "ሰባትን በሰባት አባዝተህ 490 ጊዜ ይቅር ለማለት ወስን" በማለት ስለ ይቅርታ ያስተማረው። በዚሁ ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የሚታረቁ ብቻም ሳይሆኑ "የሚያስታርቁም ጭምር ብፁዓን ናቸው" ተብሎ ተጽፏል። ብፅዕና መተርጎም የሚገባው በመንፈሳዊ ምሥጢርነቱ ብቻ ሳይሆን በእለት ተእለት የሥነ ምግባር ትምህርትነቱ (Ethical Admonition) ጭምር መሆን ይገባዋል።

**"አገር ያስ እርቅና ምክር አይጸናም"**

በአገራችን ባህሎችና ወጎች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በታሪካችን ድርሳናት ውስጥ ሳይቀር የሽምግልና አተገባበሮች፣ እርቅና ሰላም የማውረድ ተሞክሮዎችና ልምምዶች እጅግ የበዙ ናቸው። የውጭ ወራሪዎች ሉዓላዊ ድንበራችንን በደፈሩባቸው ወይንም ጥቃቶች ባደረሱብን የታሪክ አጋጣሚዎች ሁሉ የአካባቢው ተጎራባች አገራትና የሩቅ መንግሥታት ጭምር ጣልቃ በመግባት ግጭቶቹና ጦርነቶቹ በንግግርና በሰላም እንዲፈቱ የተደረጉባቸው ታሪካዊ አጋጣሚዎችም እንዲሁ በርካቶች ናቸው። ለሌሎች አገራት የውስጥና የውጭ ችግሮችም ኢትዮጵያ በአሸማጋይነትና በአደራዳሪነት የተፈለገችባቸውና የተጋበዘችባቸው እውነታዎችም እንዲሁ ዝርዝራቸው እጅግ የበዛ ነው።

የቅርብ ዘመናቱን ታሪካችንን ብናስታውስ እንኳን በወታደራዊው የደርግ መንግሥት ከሻዕቢያና ከሕወሓት ጋር የነበረው አስከፊ ጦርነት በሰላማዊ መግባባትና ሽምግልና እንዲፈታ በተለያዩ መንግሥታት፣ ቡድኖችና ግለሰቦች አማካይነት ተደጋጋሚ ጥረቶችና ሙከራዎች መደረጋቸው ይታወሳል።

የሕወሓት/አህአዴግ ሠራዊት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም አዲስ አበባን የተቆጣጠረው የደርግ መንግሥት ተደራዳሪዎች ከቡድኖቹ መሪዎች ጋር በአሜሪካው ጎምቱ ፖለቲከኛ በሚ/ር ሄርማን ኮኸን አደራዳሪነት ለንደን ከተማ ውስጥ በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ እየተነጋገሩ በነበረበት ወቅት መሆኑ ይታወሳል። ችግሮቹን በሰላምና በንግግር ከመፍታት ይልቅ የሁለቱም ወገን መሪዎች የልባቸው እብሪት "በባሩድ ጭስ" ታፍኖ ስለነበር መግባባት ሳይቻል ቀርቶ አገሪቱ እንደምን ዛሬም ድረስ ልትወጣው ወደማትችለው አረንቋ ውስጥ ተዘፍቃ አበሳዋን እንደምታይ በብዙ ማስረጃዎች ማመላከት ይቻላል። "የአንድ ቀን ስህተት ያለ ዓመት አይመዘዝ" እንዲሉም የዚያ የልብ ድንዳኔ ጦስ ትቶት ያለፈው ጠባሳና እያመረቀዘ ያለው ቁስል ዛሬም ድረስ ለፈውስ እያስቸገረን እንዳለ አኗኗራችን ምስክር ነው።

በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ሚያዝያ 28 ቀን 1990 ዓ.ም ተጀምሮ ለሁለት ዓመታት ያህል የዘለቀው አውዳሚው ጦርነትም ከሁለቱም ወገን በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች እንደረገፉበትና የየአገራቱ ኢኮኖሚ ተንኮታኩቶ ከመላሸቁ የተነሳ የሁለቱም አገራት የድህነት ደረጃ አሽቆልቁሎ "ከዜሮ በታች" በሚባልበት ደረጃ ላይ መድረሱ የጋራ መራራ ታሪካችን አካል ነው።

በታኅሳስ 3 ቀን 1993 ዓ.ም የሁለቱ አገራት መሪዎች አልጀርስ ላይ በደረሱበት "ስምምነት" መሠረት ጦርነቱ ጋብ ያለ ቢመስልም የድንበር ላይ መፋጠጡ ተጠናክሮ በመቀጠሉ ለረጅም ዓመታት "ተኩስ አልባ" ግዳጅ ላይ መከረማቸውም አይዘነጋም። በቀላል ቋንቋ መግለጽ ካስፈለገ "የዐይነ ቁራኛው ደፈጣና መፋጠጥ" እንዳለ ሆኖ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮችና በየሚዲያዎቻቸው እየተጠዛጠዙ መበሻሸቁን ተክነውበት ነበር።

ይህ ውጥረት የመቋጫ ምዕራፍ ላይ ሊደርስ የቻለው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በመጋቢት 2010 ዓ.ም ሥልጣን በያዙ በጥቂት ወራት ውስጥ ሐምሌ 2010 ዓ.ም አስመራ ከተማ በመገኘት ሁለቱን አገራት ጋርዶ የነበረው ጥቁር የጥላቻ መጋረጃ ከተቀደደ በኋላ መሆኑን ልብ ይሏል።

> **ከሰላም ስምምነቱ በኋላም በተደረሰባቸው መግባባቶች መሰረት በሁለቱም ወገኖች አበረታች ተግባሮች እየተከናወኑ ሲሆን ሕዝቡም በእፎይታ መተንፈስ መቻሉ እየተስተዋለ ነው። የትግራይን ደመና አክብዶ ሕዝቡን ለመከራ የዳረገው ስቃይም ቀስ በቀስ እየተገፈፈ ስለሆነ ሰላማዊ የሕዝብ ለሕዝብ እንቅስቃሴው በመነቃቃት ላይ ይገኛል**

**"ደም ያደረቁ አሸማጋዮች"**

"ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ" እንዲሉ፤ የኢትዮጵያ ፈተናዋ መልኩና ልኩ ይህ ዳርቻህ የሚባል ዓይነት እንዳልሆነ ለማንም ይጠፋዋል ተብሎ አይገመትም። አንደኛው አገራዊ ቀዳዳችን ሲደፈን ሌላው እየተሸነቆረ፣ የተወላገደው ሲቃና ቀናው እየጎበጠ ማማጥንና "ኤሎሄ እያሉ መቃተትን" የባህል ያህል ተቀብለን አብረን እንድንኖር የተፈረደብን ይመስላል።

ማክሰኞ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም እኩለ ሌሊት ላይ ጀግናውን፣ ርሁሩሁንና ለአገርና ለሕዝብ ሉዓላዊነትና ልዕልና መጠበቅ በግዳጅ ቀጣናው ላይ በተጠንቀቅ ቆሞ የሚታደገን የሰሜን እዝ ሠራዊት በሕወሓት ተከድቶ በኢትዮጵያ ምድር የዘነበው መከራ ገና በአግባቡ ተመዝግቦና ተተርኮ ስላልተጠናቀቀ ዝርዝሩን ለማቅረብ በእጅጉ ያዳግታል። ክስተቱ በትናንትና ጀንበር የተፈጸመ ስለሆነ የጉዳቱን ልክ እንዲህና እንዲህ ብሎ መከለሱ አስፈላጊነቱ አልታየንም።

ምን ያህል ወገን እንደረገፈ፣ ምን ያህል ሀብትና ንብረት እንደወደመ፣ በሕዝቡ ላይ የደረሰው የሥነ ልቦና ህመምና ቀውስ ጠግጎ ገና "የቁስሉ ፋሻ" ስላልተፈታና በአግባቡ ስላልተሰነደ ጊዜ ሰጥቶ መታገሱ ተገቢ ይመስለናል። ይህንን ደም ያቃባ ክስተትና በቂም የተቋጠረ ልብ በሰላማዊ ንግግር በመግባባት መፍታት እስካልተቻለ ድረስ አገሪቱ ከገባችበት አረንቋ ፈጥና እንደማትወጣ በመታመኑ ውሳኔው መራራ ቢሆንም አንድ እርምጃ ግን መወሰድ ነበረበት።

በዚሁ መሠረትም በአፍሪካ ኅብረት ስምሪት ሰጭነት በቀድሞዎቹ የናይጄሪያና የኬኒያ ፕሬዚዳንቶች በክቡር ኦሊሴንጎ ኦባሳንጆና በክቡር ኡሁሩ ኬኒያታ አሸማጋይነት በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ የሰላም ስምምነት መፈረሙ ይታወሳል። የስምምነቱን አተገባበር በተመለከተም በኬኒያ ናይሮቢ በተደረጉ የሁለት ዙር ንግግሮችና ውይይቶች አማካይነት "እርቀ ሰላም ወርዶ" የጦር መሣሪያ ላንቃዎች እንዲዘጉና ጠብ ቀስቃሽ መቆራቆዞች እንዲረግቡ ተደርገዋል።

ከሰላም ስምምነቱ በኋላም በተደረሰባቸው መግባባቶች መሰረት በሁለቱም ወገኖች አበረታች ተግባሮች እየተከናወኑ ሲሆን ሕዝቡም በእፎይታ መተንፈስ መቻሉ እየተስተዋለ ነው። የትግራይን ደመና አክብዶ ሕዝቡን ለመከራ የዳረገው ስቃይም ቀስ በቀስ እየተገፈፈ ስለሆነ ሰላማዊ የሕዝብ ለሕዝብ እንቅስቃሴው በመነቃቃት ላይ ይገኛል።

የእርቀ ሰላሙ ውጤት ከጮርቃነት ወደ ብስል ፍሬነት ጎምርቶ የተፈጠረው የታሪክ ስብራት ሙሉ ለሙሉ ተፈውሶ ጠባሳው እስኪድን ድረስ ብዙ የሚሰሩ ቀሪ አገራዊ ሥራዎች እንዳሉ አይጠፋንም። ለሰላሙ መተግበር ቀዳሚ ትኩረት ሊሰጥ የሚገባው ለፖለቲካ ውሳኔ መሆኑ ባይካድም የመንፈሳዊ ሥልጣንም ሊዘነጋ አይገባም። መላው ሕዝብ ኢትዮጵያ በጾምና በጸሎት ፈጣሪውን በመማጸን ያደረገው አስተዋጽኦ በፍጹም የሚረሳ አይደለም።

በአንጻራዊ መልኩም ቢሆን የነበረው የተካረረ ውጥረት ረግቦ "የሰላማችን ርግብ" ከቁስለቷ በማገገም የዘንባባ ቀንበጥ በአፏ እንደያዘች በሰማዩ ላይ ለመቅዘፍ እያቃሰተችም ቢሆን መብረር ጀምራለች። ሙሉ ለሙሉ ተፈውሳና ዝማሬ አክላበት በሰማያችን ላይ ደምቃ እንደምትከንፍ ተስፋ እናደርጋለን።

የኢትዮጵያ የሰላም ሁኔታ ግድ ብሏቸውና የመከራችን ክብደት ተሰምቷቸው እርቀ ሰላሙ ገቢራዊ እንዲሆን ከአገራችን ጎን የነበሩና የቆሙ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት፣ ግለሰቦችና ቡድኖች በርካቶች መሆናቸውን አንዘነጋም። በተለይም የአህጉራዊው አፍሪካ ኅብረት መሪዎችና የሰላሙን ስምምነት በስኬት እንዲያስፈጽሙ የተወከሉት ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ክቡር ኦባሳንጆ ኦሊሴንጎንና ክቡር ኡሁሩ ኬኒያታን የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ስለ ድካማቸውና አስተዋጽዋቸው በልዩ ሁኔታ ማመስገኑ አግባብ ብቻ ሳይሆን ተገቢም እንደሆን ይታመናል።

ስለዚህም ኢትዮጵያ ሆይ ስለተደረገልሽና ለእኛም ለሕዝቦችስ ስለተደረገልን መልካምነትና በጎነት አሸማጋዮቹን የሰላም መልእክተኞች በምስጋና አክብሪልን። እኛ ዜጎችም ድምጻችንን ከፍ አድርገንና እንደ ባህላችን ዝቅ ብለን አክብሮታችንን እንገልጽላቸዋለን። ለአፍሪካ ኅብረት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ ለሁለቱ አንጋፋ የአፍሪካ አባቶች እና በሰላም ስምምነቱ ሂደት ውስጥ ሚና ለነበራቸው ለበርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት በምስጋናችን ቃል ማክበራችን እንደተጠበቀ ሆኖ ውለታችሁ በትውልዶች ሁሉ ዘንድ እንዲታወስና በታሪካችን ውስጥ ጎልቶ እንዲሰነድም የተቻለውን ሁሉ ጥረት እናደርጋለን። ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

# በፈተናዎች ያልተቀለበሰ የዛሬ ማንነት

**ሰላማዊት ውቤ**

ለትምህርት ባላቸው ጽኑ ፍላጎትና ጉጉት አብዝተው ይታወቃሉ። በስምንተኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ለመጀመሪያ ጊዜ ከትምህርት ቤታቸው 100 ያመጡት እሳቸውና ጓደኛቸው ብቻ ነበሩ። ሆኖም በጥሩ ውጤትና ስሜት የጀመሩትን የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን አቋርጠው በአፈና ብሄራዊ ውትድርና ተወስደዋል። በዚህ ውስጥ እንኳን የሚጓጉለትን ትምህርት መዘንጋቱ በፍፁም አልተቻላቸውም። በውትድርናው የሚጠበቅባቸውን ግዳጅ ፈጽመው “አገር አማን” በማለት የ11ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ለመቀጠል ትምህርት ቤት ገብተው ነበር። ይሁን እንጂ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ታፍነው ወደ ውትድርና በመላካቸው ዳግም ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገድደዋል። መጀመርያውኑ ጎበዝ ተማሪ የሆኑትና የት መድረስ እንዳለባቸው አሳምረው የሚያውቁት እኚህ የዓላማ ሰው ለመማር ብዙ መስዕዋትነትን ከፍለዋል።

ሰውየው ግዳጃቸውን ለመፈፀም በከባዱ የአሰብ እና የትግራይ በረሃዎች ውጊያ ላይ ተሳትፈዋል። ለዓመታት የዘለቀ ግዳጃቸውን የጨረሱት በእነዚሁ አውሬ እንጂ ሰው በማይኖርባቸው፣ ጭው ያሉ በረሃዎች ገደላገደል ላይ ተንጠላጥለው እያደሩና እየዋሉ ነበር። በበረሃዎች ብዙ ፈተናዎች ገጥመዋቸዋል። በአሰብ በረሃ በአንድ የአዲስ ዓመት መባቻ ከአንድ ትልቅነቱን ኢትዮጵያ ውስጥ በፍፁም አይተውት ከማያውቁ ዘንዶ ከሚያክል፤ አንዳች ነገር ላይም አብዝቶ ከተጠመጠመ፤ በቀዬው መገኘታቸውን እንደ ድፍረት ቆጥሮም ተገርሞም፤ ሊበላቸውና ሊነድፋቸው ካቆበቆበ እባብ ጋር ዓይን ለዓይን ተገጣጥመዋል።

“ሰው ችግር ሲያጋጥመው የሚወጣበትንና የሚፈታበትን መንገድ ማሰብ አለበት” የሚሉት ዶክተሩ በእነዚህ ፈተናዎች ውስጥ ቢያልፉም የትምህርታቸው ነገር ስለማይሆንላቸው እንኳን ትምህርት መቀጠል፤ ማሰቡም በማይቻልበት ሁኔታ ከትምህርት ላለመራቅ ጥረት ሲያደርጉ ኖረዋል። ከእሳቸው ጋር ፉክክር የያዘ ይመስል በየዓመቱ ከፍ የሚለውን የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ለማሸነፍ እልህ ተጋብተው ከአራት ጊዜ በላይ የማትሪክ ፈተና በግላቸው ወስደዋል። በአምስተኛው አራት ነጥብ አምጥተው ዩኒቨርሲቲ መግባትና ዲግሪያቸውን መያዝ ችለዋል። የህይወት ጥሪያቸውን መስመር እስኪያገኙት ድረስ ራሳቸውን መስዕዋት ቢያደርጉም ዩኒቨርሲቲ በመግባት መስመሩን ካገኙት በኋላ ትምህርትና ሥራን ጎን ለጎን በማስኬዱ ተሳክቶላቸዋል።

ሆኖም የዛሬው እንግዳችንን ዶክተር ንጉሴ ምትኩን የትዳር አጋራቸው ባታስተምራቸው ፈተናው ይበረታባቸውና የዛሬውን ስኬት ለመጨበጥ ረጅም ጊዜ ይወስድባቸው ነበር። እንኳን መምህር ለመሆንና ኢቢሲን እና አሁን በዋና ዳይሬክተርነት እየመሩት ያለውን የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩትን ጨምሮ የተለያዩ ተቋሞችን በመምራት ለአገራቸው ዘርፈ ብዙ አስተዋጾ ሊያበረክቱ ቀርቶ ያቋረጡትን ትምህርት ለማጠናቀቅ አይበቁም ነበር። ሆኖም፣ ፈተናዎችን ተቋቁመው በማለፋቸው ከራሳቸውም አልፎ ላገለገሉባቸው ተቋማትም መትረፍ ችለዋልና በኃላፊነት በሰሩባቸው ጊዚያት ያበረከቱት አስተዋጾ ጎልቶ ይወሳል። በተለይ ገና መሰረቱ ሲጣል ጀምሮ ከሬጅስትራር ኃላፊነት እስከ ፕሬዚዳንትነት በሰሩበት በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አንድ ብቻ የነበረውን ካንፓስ በሁለትና ሦስት እንዲሰፋ ከማድረግ ባሻገር ለዘለቄታው የማይነጥፍ ገቢ ባለቤት እንዲሆንም የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል፡፡

እንግዳችን እንደሚሉት ለተማሪ ዲሲፕሊን በጣም ወሳኝ ነው። ዲሲፕሊን የሌለው ትውልድ አገርን ያፈርሳል። ያኔ እሳቸው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ዘመን እንደዚህ ዓይነት ነውጦች ተስተውለው ነበር። ችግሮቹን ለመፍታት ተማሪዎችን አቅርቦ ለማስረዳትና ለመምከርም ተሞክሯል። ወጣ ያለውንም በነበረው ጥብቅ ሕግ የመዳኘቱ ተግባር ተከናውኗል። ግን ሕጉ ተማሪን ለመጉዳት ያለመ አይደለም። በመሆኑም ያኔ የተዘረጋው አሁንም እየተሰራበት ነው ያለው። በዛሬው የሕይወት ገጽታችን ይህን የዶክተር ንጉሴን አስተማሪና አርአያነት ያለውን፤ በጽናት የታጀበ ተሞክሮ እንድትጋሩ እንጋብዛለን።

ዶክተር ንጉሴ ምትኩ ይባላሉ። የተወለዱት በድሮው አጠራር ጎጃም ክፍለ ሀገር፣ ቆላ ደጋ ዳሞት አውራጃ፣ ቡሬ ወረዳ፣ ቻባ ሚካኤል በሚባል የገጠር ቀበሌ ነው።

እዚህች ሥፍራ እንደማንኛውም ልጅ አፈር ፈጭተውና ውሃ ተራጭተው አድገዋል። የገጠር ሀብት ብዙም ባይሆንም ወላጆቻቸው የተሻለ ኑሮ የነበራቸው ናቸው። ሆኖም ዘመናዊ ትምህርት የመማር ዕድል ያገኙት እሳቸው ብቻ ነበሩ። አብዛኞቹ ቤተሰቦቻቸው ባህላዊ የቤተ ክህነት ትምህርት በመቅሰም ካህናት ሲሆኑ ዕድሜያቸው ለትምህርት ከመድረሱ ወደ ዘመናዊ ትምህርት ስለላኳቸው እንደ ብዙዎቹ የገጠር ተወላጆች የእርሻ ሥራን አልቆዩበትም። ሆኖም በልጅነታቸው በእረኝነት አልፈዋል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት በአካባቢያቸው በመሆኑም የገጠርን ሕይወት አሳምረው ያውቁታል።

እንግዳችን ዶክተር ንጉሴ ምትኩ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት “ቲሊሊ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት” ነው። ከቤታቸው ትምህርት ቤት ለመድረስ ሲሄዱ አንድ ሰዓት ተኩል፤ ሲመለሱም እንዲሁ፤ ባጠቃላይ በቀን ከሶስት ሰዓት በላይ መጓዝ ይጠበቅባቸው ነበር፤ ተወጥተውታል።

ትምህርት ቤታቸውን እሳቸውና ጓደኛቸው በስምንተኛ ክፍል አገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና በትምህርት ቤቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ 100 በማምጣት ነው የተሰናበቱት። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከዘጠነኛ ክፍል የጀመሩት ምዕራብ ጎጃም ዞን በሚገኘው የቡሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ይህ ዘመን 1977 ዓ.ም ሲሆን፣ ዘመኑ በኢትዮጵያ ታሪክ በድርቅም፣ በጦርነት ቀውስም ጎልቶ ይታወቃል። “የሀብታም ልጅ ወደ ቦሌ፤ የደሀ ልጅ ወደ ባሌ” ተብሎ ስርዓቱ በዜጎች መካከል ስለፈጠረው አድሏዊ አሰራር የሚተችበትም ነበር። ሆኖም በትምህርት ብርቱውና ታዳጊው ንጉሴ በዚህ መልኩ ከስርዓቱ አንድ አስከፊ ገጽታ በነበረው የጦርነቱ ቀውስ ሰለባ እሆናለሁ ብለው እንኳን በዕውናቸው በህልማቸውም አላሰቡም። በዚሁ ሳቢያ ከምወደውና አንደኛነትን ከምቀዳጅበት የትምህርት ገበታዬ እለያለሁ የሚል ጥርጣሬ እንኳን አልገባቸው። ምክንቱም በዕድሜም ለጦርነትም ሆነ ለዚሁ ግብዓት ለሚውል ስልጠና ይበቃሉ ተብለው የማይገመቱ፣ ገና ትንሽ ልጅ ነበሩና ነው። ሆኖም ዕጣፈንታቸው ሆነና ሳያስቡት፣ ድንገት ደርግ ለሁለተኛው ዙር ብሄራዊ ውትድርና እያፈነ ወደ ጦርነት ከሚማግዳቸው ታዳጊዎች መካከል አንዱ ሆነው አረፉት። ታፍነው በመወሰዳቸው ምክንያትም በቡሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጀመሩትን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ለማቋረጥም ተገደዱ።

“ጦላይ ውትድርና ማሰልጠኛ ማእከል” ለስድስት ወር የውትድርና ስልጠና ተከታተሉ፡፡ ሥልጠናውን አጠናቀው ወደ ትግራይ ተመድበው በዚያው ከሁለት ዓመት በላይ በሰራዊቱ ውስጥ አገልግለዋል፡፡ እዚሁ ግዳጅ ውስጥ ሆነውና እንደምንም ብለው ሳያጠናቀቁ ከዘጠነኛ ክፍል ያቋረጡትን በመጀመር የ10ኛ ክፍል ትምህርታቸውን መቐለ ከተማ ውስጥ በሚገኘው “አፄ ዮሐንስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት” ተምረዋል።

ወደ ኋላ እንደሚያስታውሱት፣ የውትድርናው ህይወት ብዙ ልምዶችን መቅሰምና ተሞክሮዎችን ማትረፍ አስችሏቸዋል። በአፈና ብሄራዊ ውትድርናን ከመቀላቀላቸው በፊትም፣ በትምህርት የታነፀ ምስጉን ስነምግባር ቢኖራቸውም ግዳጅ ላይ በነበራቸው ቆይታ የበለጠ በስነምግባር ተክነውበታል። ዕውቀት ቀስመው ተጠቅመውበታል። በልጅነታቸው ውጣውረድን እንዲያዩና የተሟላ ሰው እንዲሆኑ፤ በተለይም ደግሞ በውትድርናው ዓለም ያለውን ውጣ ውረድ እንዲረዱት፤ ልጅነታቸው እንዲጠነክርና በአዋቂ ቁመና እንዲቃኝ የበኩሉን አስተዋጾ አድርጎላቸዋል። “አሁን ላለው ስብዕናዬ እና ጥንካሬዬ መሰረት ሆኖኛል” ሲሉም ነው አጋጣሚውን የሚገልፁት።

‹‹የውትድርና ቤት ለእኔ ለሕይወቴም በጣም ጥሩ ነው። ውትድርና ትልቅ ትምህርት ቤት ነው። ወታደራዊ ሳይንስም ትልቅ ዕውቀት ነው። ምንም እንኳን ፈቅጄና ተቀጥሬ ያልሄድኩ ቢሆንም፣ አሁን ላለኝ ማንነትና ለደረስኩበት ደረጃ ጠቅሞኛል ብዬ ነው የማስበው” ሲሉ ፋይዳውን ይገልፁታል። እንግዳችን ዶክተር ንጉሴ ምትኩ ፈጣሪ ረድቷቸው ግዳጃቸውን በዚህ መልኩ ፈጽመው ወደ መጡበት ቀዬም በሰላም ተመልሰዋል። አሁንም ተስፋ ሳይቆርጡና በዕድላቸው ሳይማረሩ ያን የሚወዱትን፤ በእጅጉም የሚጓጉለትን ትምህርታቸውን ካቆሙበት መልሰው ቀጥለውት ነበር።



ፎቶ፡ ፀሀይ ንጉሴ

ዶክተር ንጉሴ ምትኩ

ነገር ግን ወቅቱ በጊዜው ስልጣን ላይ የነበረው የደርግ መንግስት ‹‹ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር›› ያለበት ነበረና ለሁለተኛ ጊዜ ከሚማሩበት ክፍል ታፍነው ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ውትድርና ተላኩ። የጀመሩት የ11ኛ ክፍል ትምህርትም በሚያሳዝን ሁኔታ ተቋረጠ። አሰብ በርሃ ውስጥ በብሄራዊ ውትድርና ግዳጅ ከሁለት ዓመታት በላይ ለማሳለፍም ተገደዱ።

ዶ/ሩ በርካታ ወታደራዊ ፈተናዎችን ተወጥተዋል። ከብዙ አውሬና አራዊቶች ጋር ተፋጥጠዋል። አሰብ እያሉ ለአራት ወር ግዳጅ አፋምቦ የሚባል ሩቅ ቦታ የገጠማቸው ሁኔታ አንዱ ማሳያ ነው።

ከእሳቸው ቁመት የሚበልጠውን ድንጋይም ደገፍ ብለው ጣፋጩን የዓውድ ዓመት ትዝታ በማጣጣም ረሀብና ጥማቸውን ለመርሳት አረፍ አሉ። ምን እንዳዘራቸው ባያውቁም አረፍ ባሉበት ቅጽበት ወደ ኋላቸው ዞር አሉ። ከኋላቸው ከተወለዱ ጀምሮ እዛ ዕድሜ ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ በፍፁም አይተውት የማያውቁት ትልቅ እባብ በብዙ ድግግሞሽ በመጠምጠም ቁጭ ካለበት አንገቱን በማቅናት እንዳፈጠጠባቸው ዓይን ለዓይን ይገጣጠማሉ። እንዴት ከተቀመጡበት ተነስተው እንደሮጡ ዛሬም እያስታውሱት። ሳይነድፋቸውና ሳይበላቸው ሮጠው ያመለጡት መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ እንኳን ድንጋጤው አለቀቃቸውም። ብርክ ይዟቸው ለረጅም ጊዜ ሰውነታቸው ይንቀጠቀጥ ነበር።

ከዚህ ሁሉ መከራና ስቃይ በኋላ ትምህርትን ካቋረጡበት መቀጠል ቀርቶ ተረጋግቶ መኖር የማይታሰብ ቢሆንም ዶክተር ንጉሴ ግን አድርገውታል። ከግዳጅ እንደተመለሱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካቋረጡበት 11ኛ ክፍል ጀምረው፣ የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በደብረ ማርቆስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቅቀዋል። ይሁንና “የሰራለትን የማያውቀው” ማትሪክ እንደጠበቁት አላስደሰታቸውም። ጊዜ ሳያጠፉ ፈጥነው ባመጡት 2 ነጥብ 8 የማትሪክ ውጤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ለመሆን የሚያስችላቸውን ስልጠና ለመውሰድ ወደ ደብረብርሃን መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ አመሩ። ለአንድ ዓመት ያህል በመምህርነት ሙያም ሰለጠኑ። ፈጥነውም የሥራ ዓለሙን ተቀላቀሉ። ተወልደው ባደጉበት ጎጃም አካባቢ በሚገኝ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ለአራት ዓመታት ያህልም አስተማሩ።

“መምህር ሆኛለሁ፤ እዚህ ድረስ ከደረስኩ ይበቃኛል” በማለት ጥረታቸውን አላቋረጡም። የማትሪክ ፈተናን በማለፍ የበለጠ የመማር ፍላጎታቸው ጨመረ። የገጠር አስተማሪነት ኑሮ ብዙም ባይመችም ናፍጣቸውን ሰፋ አድርገው በመሸመት ለተማሪዎቻቸው ከሚያደርጉት ዝግጅት ጎን ለጎን ለማትሪክ ፈተና የሚረዳቸውን ዝግጅት በኩራዝ መብራት ሲያጧጡፉት ቆዩ። ይሁን እንጂ፣ አራቱን ዓመት በዚህ መልኩ ቢያሳልፉም ውጤት አልመጣላቸው አለ። ማትሪክ ከንጉሴ ጋር ፉክክር የያዘ ይመስል እሳቸው ከፍ ያለ ነጥብ ሲያመጡ የዩኒቨርሲቲ መግቢያው ደግሞ የዚያኑ ያህል እያሻቀበ በእጅጉ ሲቸገሩ ቆዩ። የመጀመሪያውን ማትሪክ ሲወስዱ 2 ነጥብ 8 አመጡ፤ ሳያስገባቸው ቀሩ። ደብረ ብርሃን ከገቡ በኋላ ወስደው 3 ነጥብ 2 አመጡ፤ አሁን መግቢያው በመሰቀሉ ሳይገቡ ቀሩ። ከዛም 3 ነጥብ 4 አመጡ ሊሆንላቸው አልቻለም። 3 ነጥብ 6 አመጡ፤ አያስገባቸውም። በዚህ ሁኔታ ለአራት ዓመታት ያልተሳካላቸውን ውጤት በእልህ ከፍተኛ ዝግጅት አድርገው ፈተናውን ለአምስተኛ ጊዜ ወሰዱ።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



በመጨረሻም አራት ነጥብ አመጡና ዩኒቨርሲቲ መግባት ቻሉ።

እዚህ ጋር የአሁኗ የትዳር አጋራቸውና የሁለት ልጆቻቸው እናት ትልቅ አስተዋጾ አድርገውላቸዋል።

"የሚያስተምረኝ ቢኖር ሳጠና ቆይቼ ፈተናውን እወስድና ዩኒቨርሲቲ እገባ ነበር እንጂ ደብረብርሃን መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ አልገባም ነበር" የሚሉት ዶክተር ንጉሴ በኮሌጅ ውስጥ ከዛሬዋ ባለቤታቸውና ከሁለት ሴት ልጆቻቸው እናት ጋር መተዋወቃቸውንም ያወሳሉ። በስልጠና የተጀመረው ጓደኝነታቸው እየጠበቀ በ1987 ዓ.ም ወደ ትዳር አምርቶ ነበርና እኚሁ የትዳር አጋራቸው ለአምስተኛ ጊዜ ማትሪክ ተፈትነው ባመጡት አራት ነጥብ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ገብተው እንዲማሩ አደረጉ። ለአራት ዓመት ሲያስተምሩበት የቆዩትን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተማሪነት ሥራን ለቅቀው ትኩረታቸውን ትምህርታቸው ላይ ብቻ በማድረግ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እና ሥነጽሑፍ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ለመያዝ በቁ። ለዚህም ነው ዶ/ር ንጉሴ "የባለቤቴ መኖርና እኔን ማስተማሯ ኑሮዬን አቃንቶልኛል ብዬ አስባለሁ" የሚሉት።

እንግዳችን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በባለቤታቸው ወይዘሮ በላይነሽ አወቀ ድጋፍ ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከያዙ በኋላ ተመልሰው ወደ መምህርነት ሙያቸው ገቡ። ለአንድ ዓመት ያህልም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲያስተምሩ ቆዩ። በሂደቱም እራሳቸውን ለማሳደግ የሚያበቋቸውን የተለያዩ ጥረቶች እያደረጉ ነበር። ከጥረታቸው አንዱ ያኔ "የሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ" ይሰኝ በነበረውና በአሁኑ "ጎንደር ዩኒቨርሲቲ"፤ የዩኒቨርሲቲ መምህር ሊያደርጋቸው በሚችል ውድድር ላይ መሳተፍ ነበር። ከብዙ መምህራንም ጋር ተወዳደሩ። በማሸነፍም ወደ ዩኒቨርሲቲው ገቡ። የዩኒቨርሲቲ መምህርም ሆኑ።

‹‹አሁን መማር ቀላል ነው። ምክንያቱም ዩኒቨርሲቲ ገብቼ አንዴ መስመሩን አግኝቸዋለሁ›› የሚሉት ዶ/ር ንጉሴ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ እያስተማሩም ባገኙት የትምህርት ዕድል ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምጣት የሁለተኛ ዲግሪ (ኤምኤ) ትምህርታቸውን በዛው፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አግኝተዋል።

ትምህርትና ሥራን ጎን ለጎን ማስኬድ የሚቀናቸው ዶክተር ንጉሴ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን ከያዙ በኋላ በሥራ ምክንያት ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ወደ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መጡ። ሦስተኛ ዲግሪያቸውን (ፒኤች.ዲ)ም እዚሁ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተመሳሳይ የትምህርት መስክ ተምረው አጠናቀቁ። ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ከያዙ በኋላም መማር አላቆሙም፡ ፡ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የትምህርት መስክ ሌላ ሁለተኛ ዲግሪ ይዘዋል፡፡ መጀመሪያውኑ ጎበዝ ተማሪ የሆኑትና የት መድረስ እንዳለባቸው አሳምረው የሚያውቁት፤ የዓላማ ሰው፤ እራሳቸውን በትምህርት ለማበልፀግ የገጠሟቸውን ችግሮች በመፍታት ብዙ መስዋዕትነት እየከፈሉ እዚህ የደረሱት ዶ/ር ንጉሴ ከታዳጊነትና ወጣትነት ዕድሜያቸው አብዛኛውን በእንዲህ ዓይነቱ ፈታኝ ሁኔታ አሳልፈዋል። አሁን ላይ ለ19 ዓመት በመምህርነትና በአመራርነት ካገለገሉበት ከትምህርቱ ዘርፍ ወጥተው በሌላ የሥራ መስክ እያገለገሉ ቢገኙም፤ የመምህርነት ሙያቸውን ዛሬም ድረስ አብዝተው ይወዱታል። "ተማሪ ስነስርዓት (ዲሲፕሊን) ያለው መሆን አለበት" የሚሉት ዶክተሩ ለአራት ዓመት ያስተማሯቸውን፣ የአንደኛም ሆነ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎቻቸውን አብዝተው እንደሚወዷቸው፤ በዩነቨርሲቲ ቆይታቸውም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቻቸው ጥሩ መምህር እንደሆኑ በየአጋጣሚው ሲነግሯቸው እንደነበር ይናገራሉ። በዚሁ ሙያቸው በሰሩበት ዘመን ተማሪዎች ለአስተማሪ ያላቸው ክብር ትልቅ እንደሆነ ማየት ችለዋል። ለእሳቸው አስተማሪነት በጣም ጥሩ ሙያ ነው። "መምህር ከተማሪዎች ጋር ነው የሚውለው። ተማሪ ደግሞ ሁል ጊዜ መልካም ነገርን ነው ለመምህሩ የሚያሳየው" ሲሉ የመምህሩንና ደቀመዝሙሩን የግንኙነት መስተጋብር ይገልፁታል። መምህሩ ከተማሪ ጋር ሆኖ ሰርክ የሚያስበው ስለማወቅ፤ ስለመለወጥ እንጂ ሌላ አለመሆኑን ያስረዳሉ።

ነገር ግን ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በነበሩበት ወቅት ከዚህ ወጣ ያለ ተግባር ተስተውሎ እንደነበርም አልሸሸጉም። በእርግጥ ተግባሩ በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ከነበረው ጋር ሲነፃፀር እዚህ ግባ የሚባል እንዳልነበረም ያወሳሉ። ምስጢሩ ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ሕግ ጥብቅ መሆኑ እንደነበርም ይጠቅሳሉ። ሆኖም ተማሪን ለመጉዳት አይደለም። አገር ተረካቢ የመሆን ዓላማውን ስቶ የአገር

ሸክም እንዳይሆን ለማስቻል ነው። በፕሬዚዳንትነት ዘመናቸው በነበረው የቀውስና ነውጥ ወቅት ተማሪዎችን አቅርበው ለማስረዳትም፤ ለመምከርም ጥረዋል። ከዚህ ወጣ ብሎ በተቋሙ ላይ ችግር የሚፈጥረውንም በነበረው ጥብቅ ሕግ ርምጃ ወስዶ ችግሮችን መፍታት ተችሏል።

ዶክተሩ እንደሚሉት አሁን ሁሉ ነገር ፖለቲካ የሆነበት ዘመን ላይ ነን ያለነው። እንደሚታወቀው ልዩነት ፀጋ ነው። እኛ ኢትዮጵያዊያኖች ብዙ ልዩነት ያለበት አገር ነው ያለነው። የሐይማኖት፤ የብሄር፤ የቋንቋና የባህል ልዩነታችንን ለአብነት ማንሳት እንችላለን። በደንብ ከያዝነው ይሄ ሁሉ ሀብትና ፀጋ ነው። ቋንቋን ብቻ ወስደን ብናይ እኛ አገር ብዙ አገራት የሌላቸው አያሌ የምንገለገልበት ቋንቋ ያለን ሲሆን፣ ይሄ ቋንቋ ሀብታችን ነው። እኛ ግን ቋንቋውንም ባህላችንንም ፖለቲካ አደረግነው። እኛ አገር ብናውቅበትና በደንብ ብንይዘው አጠቃላይ ይሄ ያለን በሙሉ የቱሪዝም ሀብት የሚሆን ነው። እሳቸው የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ዘመን ይህ ጉዳይ ነው ወደ ዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ገብቶ የነበረው። ተማሪዎች ደግሞ የፈለገው ወደ ፈለገው የሚነዳቸውና ገና ያልበሰሉ ልጆች ናቸው። ያሉበት የዕድሜ ደረጃ የትኛው ከየትኛው ይሻላል ብለው በማመዛዘን ሊመርጡ የሚችሉበትም አይደለም።

ተማሪዎችን በደንብ ካስተማርናቸውና በተገቢው መንገድ ኮትኩተን ከያዝናቸው በፈለግነው መንገድ የምንወስዳቸው የወደፊት አገር ተረካቢዎች ናቸው።

ተማሪዎችን አንዳንዱ ያልተገባ የብሄር ፖለቲካ አጀንዳ ይሰጣቸውና መጠቀሚያና ዓላማቸውን የሳቱ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። የትምህርት ተቋሙ እንዲበጠበጥ ምክንያት ይሆናሉ።

‹‹እኔ በተማሪዎች አልፈርድም። ምክንያቱም ያሉበት ዕድሜ ገና ለጋ ነው። የፖለቲካ ብስለቱም የላቸውም። በዚህ በቅርብ ዘመን የመጡ በመሆናቸው ስለ ኢትዮጵያ

የሚያውቁትም

ብዙ አይደለም። ስለ ኢትዮጵያ ተሰብከው ያደጉም ስላልሆኑ ጥፋት ሊያጠፉ ይችላሉ›› ይላሉም ዶ/ር ንጉሤ። በደንብ ከተያዙ የአገር ገንቢዎች ወጣቶች ናቸው። በመሆኑም የመምህርነት ሙያ እነዚህን ልጆች የአገር ተረካቢ ማድረግ ይጠይቃል። በእሳቸው ዕድሜና ከእሳቸው ዕድሜ በላይ ያለ ሰው አገር እንዲቀጥል ትልቅ ኃላፊነት አለበት። ልጆችን፤ በተለይ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ወጣቶችን ከሚማሩት የቀለምና ተግባር ትምህርት ባሻገር ስለ አገር ፍቅር፤ ስለወገን፤ በስርዓት እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል። እንደሚያስታውሱት ያኔ እሳቸው ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በነበሩበት ከ2006 ጀምሮ 2010 እስኪመጣ የነበረው ዘመን የፖለቲካ ቀውስ የተካረረበት ነበር። ዩኒቨርሲቲው ላይ የሚነሳሱ ነውጥና ረብሻዎችም ነበሩ። ሆኖም ዩኒቨርሲቲው ይሄን ለመቀልበስ ብዙ ርቀት ሄዷል።

አንደኛው ተማሪዎቹ የመጡበትን ዓላማ እንዳይዘነጉ፤ ነገ ተነገወዲያ የአገር ሸክም እንዳይሆኑ፤ ሰው መሆን የሚችሉት በትምህርት እንደሆነ ለማስገንዘብ ጥረቶች ተደርገዋል። ይሄንኑም አቅርቦ ለማስረዳት፤ ለመምከር እንዲሁም ወጣ ያሉና በዚህ መገዛት ያልቻሉ የማስተካከያ እርምት እንዲወሰድባቸው ለማድረግ ተሞክሯል። ዩኒቨርሲቲው ተማሪዎቹ ከስርዓት ወጣ ሲሉ መዳኙት የሚችልበት ጥብቅ ሕግም ነበረው። ሕጉ ተማሪዎችን ለመበደልና ለመጉዳት የታሰበ አይደለም። ተማሪዎቹ የመጡበትን ዓላማ ሳይስቱና ሳይዘነጉ፤ ዓላማቸውን አሳክተው እንዲወጡ የሚያደርግ ነው። ይህ ያኔ የተዘረጋ የትምህርት ስርዓት አሁንም እየተሰራበት ነው። ምክንያቱም ለተማሪ ዲሲፕሊን በጣም ወሳኝ ነው። ይሄ የሌለው ትውልድ አገርን ያፈርሳል።


በከፍተኛ ትምህርቱ ዘርፍ በኃላፊነት እስከ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትነት አገልግለዋል። ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ክፍል ኃላፊነት የጀመሩት ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከሄዱ ጀምረው በሁሉም የኃላፊነት ዘርፎች አገልግለዋል። ከሬጅስትራር ኃላፊነት እስከ ዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንትነትና የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትነት ድረስ በከፍተኛ ኃላፊነት አገልግለዋል። ‹‹ሰው የበላይ ኃላፊ ሲሆን ሁሉንም ነገር ያውቃል ማለት አይደለም። ጎንደር ዩኒቨርሲቲ የክፍል ኃላፊ ሆኜ ስመደብ ደብዳቤ እንዴት እንደሚመራ አላውቅም ነበር›› የሚሉት ዶ/ር ንጉሴ ደብዳቤ እንዴት እንደሚመራና አንዳንድ ተያያዥ ነገሮች ያስተማረቻቸው ፀሐፊያቸው እንደሆነችም ያስታውሳሉ። "ከዛ በኋላም ከብዙ ሰው ተምሪያለሁ" ሲሉም ያስታውሳሉ። በቆይታቸው ከጎናቸው፣ እንዲሁም ከበታቻቸው ካሉ የሥራ ባልደረቦቻቸው ሲማሩ መቆታቸውንም አይዘነጉም። ካለቆቼም ብዙ ተምሪያለሁም ነው የሚሉት። በኃላፊነት ዘመናቸው "የማውቀውን፣ ልሰራው የምችለውን በሙሉ ሰርቻለሁ ብዬ አስባለሁ" ይላሉም። በተለይ ከምስረታው ጀምሮ በተለያየ እርከን የኃላፊነት ደረጃ ይሰሩበት በነበረው ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እንዲለወጥ የሚችሉትን ሁሉ አድርገዋል። "በኃላፊነቴ ከፍተኛ አስተዋጾ አበረከትኩ የምለውም ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ነው"ም ይላሉ።

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከየካቲት 1999 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ሲጀምር እሳቸው ሚያዝያ ላይ ነበር ወደ ዩኒቨርሲቲው የመጡት። ተቋሙ ሲመሰረት የአሰራር ስርዓቶች፤ መመሪያዎች፤ ማንዋሎች በአጠቃላይ አንድ የአካዳሚ ተቋም የሚመራበት ምንም ሕግና ሲስተም አልነበረም። ይሄን ሁሉ እያሟሉ በመሄዱ ሂደት እሳቸው ተሳታፊ ነበሩ። ስትራቴጂክ ፕላን ሲታቀድ፤ የተለያዩ የአካዳሚክ መመሪያዎች ሲወጡ፤ የአካዳሚክ ሕግ ሲወጣ፣ ብዙ የአሰራር ስርዓቶች ሲወጡ የቡድን አባልም፣ ሰብሳቢም በመሆን ተሳትፈዋል። "ከጅማሮው ጀምሮ የኔ አስተዋጾ አለበት ብዬ አስባለሁ" የሚሉትም ለዚህ ነው። በተለይ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንትና ፕሬዚዳንት ሆነው በሰሩበት ጊዜ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ከፍተኛ አስተዋጾ አድርገዋል። ለምሳሌ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዋናው አንድ ካንፓስ ብቻ ነው የነበረው። ምክትል ፕሬዚዳነት ሆነው የፕሬዚዳንትነቱንም ኃላፊነት በውክልና በያዙበት ወቅት የመማር ማስተማሩን ሂደት በስፋት ማስኬድ ያስችል ዘንድ ቡሬ ላይ ሁለተኛ ካንፓስ እንዲከፈት አድርገዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነውም በወቅቱ ከነበሩት ፕሬዚዳንትና ሌሎች የስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ማርቆስ ላይ ያለውን ሶስተኛውን የጤና ካንፓስ አስጀምረዋል። ዩኒቨርሲቲው በሚገኝበት ደብረማርቆስ ከተማ ውስጥም ሁለት ቦታዎች ላይ ሥራን ማሳለጥ የሚያስችሉ ህንፃዎች አስገንብተዋል። አንዱ ለሆቴል አገልግሎት የሚውልና ባለስድስት ወለል ትልቅ ህንፃ ሲሆን፤ ሌላኛው ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የተለያዩ ሥራ ፈጠራ ተግባራት የሚያገለግል ባለስድስት ወለል ነው። ምንም እንኳን ገና ግማሽ ላይ ሲደርስና ሳይጠናቀቅ ቢወጡም ይሄን የግንባታ ሥራ ያስጀመሩትም እንግዳችን ናቸው።

ሌላው እንግዳችን ለደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ካደረጉት ዋና ዋና አስተዋጾ የሚያነሱት አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና ብቻ ሳትሆን የኢትዮጵያም ዋና ከተማ እንደመሆኗ መጠን፣ ማርቆስም ሆነ ሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች በፌዴራል መንግስት ሥር እንደመሆናቸው የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች የተለያዩ የሥራ ተግባራትን ለማከናወን አብዝተው ይመላለሱባታል። በተለይ የትኛውም ትልልቅ የዩኒቨርሲቲው ግዥዎች አዲስ አበባ ነው የሚከናወኑት። ለግዢ የሚመጡትም ሰራተኞች የሚያርፉት በከተማዋ ነው። ነገር ግን፣ ዩኒቨርሲቲው በዚህ በኩል ከባድ ችግሮች ነበሩበት። በመሆኑም በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትነት ዘመናቸው ለዚህ አገልግሎት ይውሉ ዘንድ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሁለት ቦታዎች በጨረታ እንዲገዙ አድርገዋል። አንዱ ባለ አራት ፎቅ ትልቅ ህንፃ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲገዛ የሆነውና ኮተቤ 02 ያለው ሲሆን፣ አሁን ላይ እየተከራየ ትልቅ ገቢ እያስገኘ ነው። ሁለተኛው ከጳውሎስ ሆስፒታል በላይ የሚገኝ ሰፊ ጊቢ ነው። አሁን ላይ ይህ ጊቢ እንደ "ገስት ሀውስ" (እንግዳ ማረፊያ) ሆኖ ለዩኒቨርሲቲው እያገለገለ ይገኛል። ዶ/ር ንጉሴ አሁን እየመሩት ባለው የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩትም የራሳቸውን አሻራ ለማሳረፍ እየተጉ ይገኛሉ። ወደ ተቋሙ ተመድበው የመጡት በቅርቡ ቢሆንም ስድስት ወር ባልሞላ የስራ ዕድሜያቸው ካቀዱት ከ90 በመቶ በላዩን መፈፀም ችለዋልና አርአያነታቸው ጉልህ ነው እንላለን።

# ለቱሪዝም ዘርፉ የተሰጠው ትኩረትና ምጣኔ ሃብታዊ ተፅእኖው

**ዳግም ከበደ**




መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በቱሪዝም ዘርፍ እንደ አገር ያለን ሀብት በርካታ ነው። ይህ ሃብት ሌሎች አገራት እንዳላቸው ከፍተኛ የነዳጅ ክምችት ሊታይ የሚችል ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የተፈጥሮ፣ የባህል፣ ቅርስ፣ የፌስቲቫል፣ የታሪክና የአርኪዮሎጂ ሃብቶች ገና በሚፈለገው ልክ ያልለሙና በቀጥታ ወደ ህብረተሰቡ ኪስ ውስጥ ገብተው ምጣኔ ሃብቱን ማነቃቃት ደረጃ ላይ ያልደረሱ ናቸው። የቱሪዝም ሃብት በምጣኔ ሃብቱ ላይ ቀጥተኛ ተፅእኖ እንዲፈጥርና ህብረተሰቡን እንዲጠቅም በማድረግ በኩል በቅድሚያ ሃብቱን የመለየት፣ የማስተዋወቅና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለውጤቱ ርብርብ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በምሳሌነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት በአዲስ አበባ ከተማ ከተገነቡት የቱሪዝም መዳረሻዎች መካከል የእንጦጦ ፓርክን ብንመለከት ከግንባታው ቀደም ብሎ ጎብኚዎች ትኩረት የሚያደርጉት ዳግማዊ ሚኒሊክ ቤተመንግስትና የእንጦጦ ማሪያም ቤተክርስቲያን ላይ ነበር። አሁን ግን በተለይ የአገር ውስጥ ጎብኚዎች በዚያው አካባቢ በተገነባው የመዝናኛ ቦታዎች ላይ በብዛት እየተገኙ ናቸው። በአካባቢው በስፍራው ካሉ ታሪካዊ ቦታዎች በተጨማሪ የልማት ስራዎች በመከናወናቸው ህብረተሰቡን በቀጥታ መጥቀም እንደጀመረም የሚያሳይ ምሳሌ ነው።

የዝግጅት ክፍላችን በቱሪዝም ዘርፉ የሚከናወኑ ተግባሮች በቀጥታ ማህበረሰቡ ላይ ተፅእኖ እንዲኖራቸው ለማስቻል መከናወን ስላለባቸው ተግባራት ከቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት የቱሪዝም ዘርፍ ኃላፊና መምህር አቶ አብይ ንጉሴ ጋር ጥቂት ቆይታ አድርጎ ነበር።

"በእንጦጦ የመዝናኛ ፓርክ ውስጥ አዲስ የመስህብና የቱሪዝም መዳረሻ ከመፈጠሩም በተጨማሪ ለሥራ እድል ፈጠራው ትልቅ ድርሻ ወስዷል" የሚለው የቱሪዝም መምህሩ አብይ፤ በተመሳሳይ በከተማዋ የተገነቡትና ታድሰው ለእይታ የበቁት የቱሪዝም መዳረሻዎች ቱሪዝም ለኢኮኖሚው ያለውን ጉልህ አበርክቶ በምሳሌነት ማሳየት የቻሉ እንደሆኑ ይገልፃል። ይህ የሚያሳየው የመስህብ ስፍራዎች፣ የተፈጥሮ ሃብቶች፣ ቅርሶችና መሰል መዳረሻዎች የቱሪዝም ምርት መሆን ሲችሉና በገበያው ላይ ሲቀርቡ በማህበረሰቡ ላይ በቀጥታ የሚፈጥሩትን በጎ ውጤት ማየት እንድንችል ያደርገናል ይላል።

በዚህ መሰረት በቅርብ ግዜ ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እያገኙ የመጡ የቱሪዝም መዳረሻዎች (የጨቄ ተራራ ሙሉ ኢኮ ሎጅ፣ የአፋርና በአማራ ክልል የሚገኙ) በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት የሚታወቁ የመስህብ ስፍራዎችንም በተመሳሳይ መልኩ መንግሥት በልዩ ሁኔታ በመደገፍ ህብረተሰቡ ላይ ቀጥተኛ በጎ ተፅእኖ እንዲያመጡ መስራት እንደሚያስፈልግ መምህሩ አብይ ንጉሴ ይናገራል። በተለይ መንገድን የመሰሉ መሰረተ ልማቶች በአገር አቀፍ ደረጃ ሲሰሩ የተፈጥሮ፣ የባህልና የታሪክ ሃብቶች ያሉበትን አካባቢም ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሰራት እንዳለባቸው በመግለፅም ዘርፉን የሚመራው የቱሪዝም ሚኒስቴርም ሆነ ተጠሪ ተቋማት ለተፈፃሚነቱ በትኩረት ሊሰሩ እንደሚገባ በምክረ ሃሳብ ደረጃ ያስቀምጣል።

"የመሰረተ ልማት በአግባቡ ከሰራን፣ ሃብቶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ ከቻልንና ወደ ቱሪዝም ምርትነት ከቀየርናቸው ሃብቶቻችን 'የጋን ውስጥ መብራት' አይሆኑም" የሚለው የቱሪዝም ትምህርት ክፍል ኃላፊውና መምህር አብይ ንጉሴ፤ የምጣኔ ሃብትን ጠቀሜታ ብቻ ሳይሆን ገፅታችንን ለመገንባት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጠቅሙን ይገልፃል። የመስህብ ሃብቱን ወደ ቱሪዝም ምርትነት ከተቀየረ በኋላም በቅርቡ "ልወቅሽ ኢትዮጵያ" በሚል የአገር ውስጥ ጎብኚዎችን ለማነቃቃት በዓለም ዋንጫ ወቅት እንደተካሄደው ሁሉ የማስተዋወቅና የጉብኝት ልምድ እንዲመጣ የማበረታታት ሥራ መቀጠል እንደሚኖርበት ምክረ ሃሳቡን ይሰጣል።

ዛሬ ኢትዮጵያ ያለችበትን የምጣኔ ሃብት (ጂዲፒ) ደረጃ አይተን ተስፋ ልንቆርጥ አይገባም የሚለው ምምህር አብይ ንጉሴ፤ ከ100 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ያላት ኢትዮጵያ የሳይንስ ሙዚየም፣ እንጦጦ ፓርክ፣ የገበታ ለአገር ፕሮጀክቶችና ሌሎችም የቱሪዝም መዳረሻ ልማት በአግባቡ ከሰራችና ወደ ምርትነት ከቀየረች ከዓለም አቀፍ ቱሪስቱ በላይ በአገር ውስጥ ያሉ ዜጎችን ብቻ ተጠቅሞ ዘርፉን ማነቃቃትና የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ያስረዳል። ይህንን አቅምም ሳይውል ሳያድር መጠቀምና በጥንካሬ መስራት እንደሚያስፈልግ ነው የዘርፉ ምሁር የሚናገረው።

"የቱሪዝም መዳረሻ ልማት ሥራዎችን ስንሰራ የምናወጣውን ከፍተኛ ወጪ መመልከት የለብንም" የሚለው መምህሩ፤ ከፍተኛ ወጪም ቢሆን ትክክለኛው ልማት ላይ ካዋልነው የቱሪዝም ዘርፉ በአጭር ግዜ ውስጥ ወጪዎችን የሚመልስና ተጨማሪ የአገር ሃብትን የሚፈጥር እንደሆነ ይናገራል። እንደ ምሳሌም ከፍተኛ ወጪ ተደርጎባቸው የተሰሩት የወዳጅነት ፓርክ፣ ቤተመንግስት፣ እንጦጦ ፓርክና መሰል የቅርብ ግዜ መዳረሻዎች በፍጥነት በብዙ ህዝብ እየተጎበኙና ገቢ እያስገቡ መሆናቸውን ልንረዳ ይገባል ይላል። በዚህ ምክንያት መልሶ የሚከፍለው የቱሪዝም ዘርፍ ላይ መዋለ ንዋይ ለማፍሰስ መንግሥትም ሆነ የግሉ ዘርፍ አንቀሳቃሾች ጥርጣሬ ውስጥ ሊገቡ እንደማይገባ ያስረዳል።

**የማስተዋወቅና ገበያ ልማት**

"የመስህብ ሃብቶቻችንን በማስተዋወቅ ረገድ ጥንቃቄ ልንወስድ ይገባል" የሚለው መምህሩ፤ 'ከፈረሱ ጋሪው ቀደመ' እንደሚባለው ብሂል እንዳይሆን ማስተዋል ያስፈልጋል ይላል። አንድን የመስህብ ስፍራ ስናስተዋውቅ ለአገር ውስጥም ሆነ ለዓለም አቀፍ ጎብኚዎች 'ቃል' እየሰጠን መሆኑን አንስቶ አስፈላጊው የመሰረተ ልማት ሥራ ሳይሟላ፣ ሃብቱ በሚገባ ወደ ቱሪዝም ምርትነት ከመቀየሩ አስቀድሞ ማስታወቂያው ገንኖ እንግዶች ቢመጡ ገፅታን የሚያበላሽና ከውጤት ይልቅ አሉታዊው ተፅእኖ የጎላ እንደሚሆን ይናገራል።

በመሆኑም ሁሉንም መስፈርቶች አሟልቶ ወደ ማስተዋወቅ ሥራው መግባት አስፈላጊ መሆኑን ይመክራል። በተሟላ መልኩ የሚተገበር የቱሪዝም ሥራ ደግሞ ከዋና ዋናዎቹ የምጣኔ ሃብት አንቀሳቃሽ አንዱ ፈር የሚቀድ እንዲሆን ያስችላል የሚል እምነት አለው።

ከላይ ባነሳነው ምክንያት የገበያና ማስታወቂያ ልማት ከመሰረታዊ የመሰረተ ልማት ሥራ መቅደም እንደሌለበት የቱሪዝም ባለሙያው ምክረ ሃሳብ ይሰጣል። በሌላ መልኩም አንድ ዓለም አቀፍ ጎብኚም ሆነ የአገር ውስጥ ዜጎች ካሉበት ስፍራ ወደ መስህብ ስፍራዎች ሲያቀኑ ቆይታቸውን ማራዘም እንዲችሉ የሚገፋፉ አገልግሎቶችን (የደህንነት ጥበቃ፣ አልጋ፣ መፀዳጃ፣ ሬስቶራንትና ሌሎች የቱሪዝም ምርቶች) ማግኘት እንደሚገባቸው ይገልፃል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ለቱሪዝም መዳረሻ ምቹ የሆኑ ስፍራዎችና የታሪክ፣ የተፈጥሮ፣ ቅርስና መሰል ሃብት ያለባቸው አካባቢዎችን በስፋት ማስተዋወቅ የሚገባውና እንግዶችን መጋበዝ የሚያስፈልገው የተነሱት አስፈላጊ መሰረታውያን ከተሟሉ በኋላ እንደሆነ ይናገራል። በምሳሌነት ደብረ ሊባኖስን አንስቶም በዚያ የኢትዮ ጀርመን ሬስቶራንትና መሰል የአገልግሎት መስጫ በመኖሩ ተመራጭ እንደሆነ ያነሳል።

"ዘርፉን በሚመሩ የግሉም ሆነ የመንግሥት አካላት አሁን ላይ እየተዋወቁ ያሉ የኢትዮጵያ የመስህብ ሃብቶች ሁሉም ከላይ ያነሳነውን መስፈርት አሟልተዋል ማለት አይቻልም" የሚለው መምህሩ፤ የመሰረተ ልማት እና የመዳረሻ ልማት በበቂ ሁኔታ ያላቸው ቢኖሩም እንኳን ሁሉም እዛ ደረጃ ላይ ደርሰዋል ማለት አንደማይቻል ነው የገለጸው፡፡ ሃብቶቹ መኖራቸውን ግንዛቤ መፍጠርና ማሳወቅ ተገቢ ቢሆንም በቂ መሰረተ ልማት ሳይሟላ በተለይ ዓለም አቀፍ ጎብኚዎችን ወደዚያ አካባቢ መጋበዝ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ያነሳል።

**የማህበረሰብ አቀፍ ሎጅ፣ መሰረተ ልማትና የምጣኔ ሃብት እድገት**

የቱሪዝም መዳረሻ ልማት ሲከናወን የአካባቢውን የተፈጥሮ፣ ባህልና መሰል ገፅታዎች በማያበላሽ መልኩ መሆን እንዳለበት የዘርፉ ባለሙያዎች ይመክራሉ። ይህንን ሃሳብም በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት የቱሪዝም ዘርፍ የትምህርት ክፍል ኃላፊና መምህር አብይ ይጋራዋል።

"የማህበረሰብ አቀፍ ሎጅ የአካባቢው ነዋሪዎች ለመስህብ ሃብቶቹ የኔነት እንዲሰማቸው የሚያደርጉ ናቸው" የሚለው መምህር አብይ፤ ዜጎች በሃብቱ ላይ 'የእኔነት' ስሜት አሳደሩ ማለት መዳረሻውን ለመጠበቅና የእንግዶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ሁነኛ መንገድ እንደሆነ ይናገራል። በተጨማሪ በዙሪያው ያለው ነዋሪው የመስህብ ስፍራውን ለመመልከት ከሚመጡ የአገር ውስጥም ጎብኚዎች ምጣኔ ሃብት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይናገራል። ከዚያ በላይ ግን የማህበረሰቡ ቱባ ባህል፣ አኗኗርና አጠቃላይ ማንነት ለማሳየትና ሳይበረዝ ለጎብኚዎች ለማቅረብ ምቹ አጋጣሚ እንደሆነ ይናገራል። በዚህ ምክንያት የማህበረሰብ አቀፍ ሎጆችን ማስፋት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው አያሌ መሆኑን ያስረዳል።

"ማህበረሰቡ በአካባቢው ላይ በሚካሄድ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ላይ ተሳታፊ ካልሆነ አለመስማማት/ 'antagonistic society' /እንዲፈጠር ያደርጋል" የሚለው መምህር አብይ፤ ቀጥተኛ የምጣኔ ሃብት ተጠቃሚ ካልሆኑና ጥቅሙን ካልተረዱ የልማቱና የዘርፉ ተቃዋሚ እንደሚሆኑ ይናገራል። ከዚህ መነሻ የማህበረሰብ አቀፍ ሎጅና የቱሪዝም መዳረሻ ልማቶችን ማስፋፋት ይህንን አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያስቀርና ማህበረሰቡን የሃብቱ ተጠቃሚና ባለቤት እንደሚያደርግ ይናገራል። በመሆኑም በዚህ ንኡስ ዘርፍ ላይም መስራት ተገቢ መሆኑን ያሳስባል።

**የሙያ ብቃትና የዘርፉ ማነቆዎች**

የቱሪዝም ዘርፍ ከዋና ዋና የምጣኔ ሃብት ምሰሶዎች ውስጥ ተመድቦ በመንግሥት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል። የልማት፣ የገበያና ፕሮሞሽን በመስራት፣ አካታች ቱሪዝምን ተግባራዊ በማድረግ አሁን ካለበት ደረጃ ለማሻሻልና የታለመለትን ግብ ለማሳካት ደግሞ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማብቃት የሚጠይቅ ነው። በሆቴልና ሆስፒታሊቲ እንዲሁም በአገልግሎት ዘርፉ ላይ ብቁ ባለሙያዎች የማሰማራት ችግር እንዳለና የሙያው ባለቤት የሆኑትም የተግባር ሥራው ላይ ደካማ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ አንዳንድ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ይህንን ሃሳብ ያነሳንላቸው የማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩቱ የቱሪዝም ዘርፍ ምምህርና ኃላፊ እንደሚከተለው ሃሳባቸውን ይሰነዝራሉ።

"ባለሙያዎችን ከማብቃት አንፃር ተግባራዊ ልምምድ ላይ አንዳንድ ጊዜ ትኩረት አለመስጠት ይታያል" የሚለው መምህር አብይ፤ ይሁን እንጂ በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት ቱሪዝምን በሚመለከት በሚሰጡ የትምህርት አይነቶች ላይ ተማሪዎች ጉዞ አድርገው "ትምህርታዊ ጉብኝት" የሚያደርጉበት እንደሆነ ይገልፃል። በተለይ በሆቴል ዘርፍ ወደ መስክ እየወጡ በተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት አግባብ እንዳለ ይናገራል። መንግስት አሁን ለዘርፉ ከሰጠው ትኩረት አንፃር ኢንዱስትሪውን የማይጠቅም የትምህርት አይነት ተቋማት የሚሰጡ ከሆነ እንዲቀር አስገዳጅ አቋም መያዙን ጠቅሶ፤ ይህንን አይነት አመለካከትና ውሳኔ ላይ መድረሱ ተገቢና ብቁ ባለሙያን ለማፍራት በሚደረገው ሂደት ላይ ድጋፍ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን አንስቷል።

በቱሪዝም የሙያ ስልጠና ላይ ከ40 በመቶ በላይ የሚሆነው ስልጠና የሚሰጠው "በትብብር ስልጠና" ማእቀፍ መሆኑን የሚያስረዳው መምህሩ፤ ይህን መሰል ተሞክሮ በሌሎች መሰል ማሰልጠኛዎች ጋር እየተስፋፋ መሄድ እንዳለበት ምክረ ሃሳባቸውን ይሰጣል። ይህን ተግባር ላይ ማዋል ከተቻለም መንግሥት እየተከተለ ያለውን ፖሊሲ ለመደገፍና የቱሪዝም ዘርፉ የአገሪቱ የምጣኔ ሃብት ምሰሶ እንዲሆን የማይተካ ሚና እንደሚጫወት ነግሮናል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## በልደቱም፣ በሞቱም፣ በዘፈኑም የበዓል አድማቂው የሙዚቃ ንጉሥ

የዚህ ሰው ነገር ይገርማል! ከውልደቱ ይጀምራል። የተወለደው በዕለተ መስቀል መስከረም 17 ቀን ነው። ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ደግሞ የፋሲካ በዓል ዕለት ሚያዚያ 11 ቀን ነው። የዚያን ዓመት የፋሲካ በዓል በሀዘን ድባብ የተዋጠ እንዲሆን አድርጎታል። በዘፈኑ ደግሞ በዓላትን ሲያደምቅ ኖሯል። በሕያው ሥራው የወደፊት በዓላትንም ያደምቃል። ይህ ሰው የሙዚቃው ንጉሥ የክብር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ነው።

ጥላሁን ገሠሠ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ከ14 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሚያዚያ 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፋሲካ በዓል ነው። የፋሲካ በዓል ቀኑ ስለሚቀያየር በዓመቱ ሚያዚያ 11 አይሆንም። የ2001 ዓ.ም የፋሲካ በዓል የተከበረው በጥላሁን ገሠሠ ሞት ሀዘን ነው። ያም ሆኖ ግን የጀግና ሞት ሀዘን አይደለምና መገናኛ ብዙኃንን ለአንድ ሳምንት ያህል በአንድ ጉዳይ ብቻ አድምቆ ይዞ ቆይቷል። ሥርዓተ ቀብሩም የተፈጸመው ለሳምንት ያህል ሰፊ ሽፋን ከተሰጠው በኋላ ነው።

የ14ኛ ዓመት የጥላሁን ገሠሠን የሙት ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ ከሕይወትና ሥራዎቹ ጥቂቶችን እናስታውስ።

ጥላሁን ገሠሠ ከእናቱ ከወይዘሮ ጌጤ ጉርሙ እና ከአባቱ ከአቶ ገሠሠ ንጉሤ በአዲስ አበባ ልዩ ስሙ ጠመንጃ ያዥ እየተባለ ከሚጠራው ሰፈር መስከረም 17 ቀን 1933 ዓ.ም የመስቀል ዕለት ተወለደ። ዕድሜው 14 ዓመት እንደሆነ ከአያቱ ጋር እንዲኖር ወደ ወሊሶ ተወሰደ፤ ራስ ጎበና በሚባለው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርት ጀመረ።

በትምህርት ቤት ሳለ፤ ጥላሁን ከፍተኛ የሆነ የሙዚቃ ፍቅር እያሳየ መጣ። አያቱ ግን ትኩረቱን በሙሉ በትምህርቱ ላይ እንዲያደርግ ይመከሩት ነበር። የራስ ጎበና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ የነበሩት ሱዳናዊው አቶ ሼዳድ ደግሞ የጥላሁንን የሙዚቃ ፍቅር በማየት ወደ ሱዳን



**ጥላሁን ገሠሠ**

እንዲሄድና በዚያም ሙዚቃ እንዲያጠና ይመክሩት ነበር። ጥላሁን ወደ ሱዳን ባይሄድም ምክራቸውን ግን ትልቅ ቦታ ስጥቶት ነበር።

ከአገር ፍቅር ቲያትር ንጋትዋ ከልካይ እና ኢዮኤል ዮሐንስ ሌሎችም የአገር ፍቅር ተዋንያን በትምህርት ቤታቸው ትርኢት ሊያሳዩ በመጡ ጊዜ፤ ይህን እድል በመጠቀም ጥላሁን ለሙዚቃ ያለውን ፍቅር ኢዮኤል ጋር ባደረገው ውይይት በሙዚቃ መግፋት ከፈለገ ወደ አዲስ አበባ መሄድ እንዳለበት መከሩት። ጥላሁን ትምህርቱን አቋርጦ ጉዞውን ወደ አዲስ አበባ አቀና። ኩብለላውን በእግር የጀመረው ለአያቱ ሳይነግር ስለነበር ከቤት ሲጠፋ አያቱ ለአጎቱ ሁኔታውን በመንገር ጥላሁንን ይጠብቁ ጀመር። ጥላሁንም የአሥራ አምስት ኪሎ ሜትር መንገዱን ጨርሶ ቱሉ ቦሎ ደረሰ፤ ከዚያም ከአክስቱ ከወይዘሮ ተመኔ ባንቱ ቤት አድሮ ወደመጣበት ወደ ወሊሶ አያቱ ዘንድ ተይዞ ተመለሰ ።

በሙዚቃ ፍቅር በጣም የተቃጠለው ጥላሁን አያቱ ቤት አንድ ቀን ብቻ በማደር ጉዞውን እንደገና ወደ አዲስ አበባ አቀና፤ በዚህ ጊዜ ግን በጭነት መኪና ላይ በመንጠልጠል ነበር። ጥላሁን አዲስ አበባ እንደገባ በአገር ፍቅር ቲያትር ቤት ተቀጠረ። በዚያም ጥቂት ዓመታት ከሰራ በኋላ ወደ ክብር ዘበኛ ባንድ በመቀላቀል እነሆ ታዋቂና ዝነኛ ለመሆን በቃ።

በ1953 ዓ.ም የታሕሣስ ግርግር ትልቅ ችግር ውስጥ ወድቆ ነበር። ለጥቂት ጊዜም ታስሮ ተፈቷል። ከዚያም ወደ ቀድሞው አገር ፍቅር በመመለስ ተወዳጅና ታዋቂ ለመሆን በቅቷል። ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ አገር ፍቅር ቲያትር ቤትን በጎበኙበት ጊዜ ሦስት ጊዜ ወጥቶ ዘፍኗል፤ ንጉሠ ነገሥቱም ‹‹ጥሩ ድምጽ አለህ፤ እንዳታበላሸው›› የሚል አስተያየትም እንደሰጡት ይነገራል።

ከጥላሁን ዘፈኖች አብዛኞቹ የአማርኛ ሲሆኑ፤ የተወሰኑ ዘፈኖችን ደግሞ በኦሮምኛ እና በሱዳንኛ ዘፍኗል። ጥላሁን ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ላደረገው አስተዋጽኦ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ተሰጥቶታል። ከኢትዮጵያ ኪነጥበብና የብዙህን መገናኛ ሽልማት ድርጅት የሙሉ ዘመን ሽልማት ተሸላሚ ሆኗል።

ትንፋሼ ተቀርጾ ይቀመጥ ማልቀሻ
ይህ ነው የምትኩለት የኔ ማስታወሻ
ውበቷን ሳሞግስ የለምለም አገሬን
ማንም አይዘነጋም በጩኸት መኖሬን!
ዜማ እንጉርጉሮዬም የግሌ ቅላጼ
ተቀርጾ ይቀመጥ ታሪኬ ነው ድምጼ
ያስቀየምኩት ቢኖር የጠላኝ በቁሜ
ድምጼን ሰምቶ ያዝናል ለረገፈው አጽሜ
እኔን ለበደሉኝ ሰርዣለሁ ቂሜን
በኔም የከፋችሁ ይቅር በሉት አጽሜን!

## ስንዱ ገብሩ

የክብር ዶክተር የሆኑት ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ የተወለዱት ጥር 6 ቀን 1908 ዓ.ም በቀድሞው አጠራር በሸዋ ክፍለ አገር በመናገሻ አውራጃ በአዲስ ዓለም ከተማ ነው። አባታቸውም ታዋቂው ዲፕሎማት፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት እና የጎንደር ከተማ አስተዳዳሪ የነበሩት ከንቲባ ገብሩ ናቸው።

ስንዱ እድሜዋ ለትምህርት በደረሰበት ወቅት ከቤታቸው አስተማሪ ተቀጥሮላቸው የአማርኛን ትምህርት ከፊደል መቁጠር እስከ ዳዊት መድገም በቤታቸው ተምረዋል። ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ሄደው በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት በመግባት እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምረዋል።

አባታቸው ከንቲባ ገብሩ ስንዱን እያስከተሉ ወደ ቤተ መንግሥትም ሆነ ሌላ ሥፍራዎች ይወስዷቸው እንደነበረና ከጊዜው አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ጋር እንዳስተዋወቋቸው ስለ ስንዱ የተጻፉ ሰነዶች ያሳያሉ። አልጋ ወራሹም የወጣቷን ብልህነትና ትጋት በማድነቅ ወደ ፈረንጅ አገር ተልከው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ባዘዙት መሠረት ወይዘሮ ስንዱ በ1921 ዓ.ም ወደ ስዊስ ለትምህርት ቢሄዱም ኑሮው ስላልተመቻቸውና ትምህርት ይሰጥበት የነበረውን የጀርመንኛ ቋንቋ ስላልወደዱት ወደ ፈረንሳይ አቅንተው ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

በመጨረሻም በስዊስ እና በፈረንሳይ ሁለት ትምህርት ቤቶች በመዘዋወር በዲፕሎማ ተመረቁ። እዛው የሕግ ትምህርት ለመቀጠል ጀምረው የነበረ ቢሆንም፤ ፍላጎታቸው ወደ ሥነ ጽሑፍ በማዘንበሉ በአጠቃላይ ለአምስት ዓመታት እዚያው ተምረው ወደ አገራቸው ተመለሱ።

የጣሊያን ፋሺስቶች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ ወይዘሮ ስንዱ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እና ሆለታ ውስጥ ከሚገኙ ወደ መቶ የሚጠጉ የጦር መኮንኖች ጋር ተቀላቅለው ፋሺስቶችን ለመፋለም ወደ ቦሬ ሄዱ። እዚያም የመትረየስ አተኳኮስ ትምህርት ተማሩ። ወደ ነቀምት በመሄድም ሕዝብን እየሰበሰቡ ስለ ነፃነት ማስተማሩን ተያያዙት። በዚህ ወቅት በባንዳዎች ጠቋሚነት በፋሽስት እጅ ከመውደቅ ለጥቂት አምልጠው ጎሬ ላይ ከልዑል ራስ እምሩ ጦር ጋር ተቀላቀሉ። ከዚያም በጦርነቱ የሚጎዱ አርበኞችን ለማከም የሚሆን ቀይ መስቀል ለማቋቋም መፈለጋቸውን ለራስ እምሩ አማክረው በተሰጣቸው 500 ብር አቋቁመው አርበኞችን መርዳት ጀመሩ። ወዲያው ግን እርሳቸው ተቀላቅለውት የነበረው የጥቁር አንበሳ ጦር ሲመታ በጣልያን ሠራዊት እጅ ተማርከው በእስር ወደ አዲስ አበባ አምጥተዋቸው የቁም እስረኛ ሆነዋል።

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ግራዚያኒን ለመግደል በተደረገው ሙከራ ወንድማቸው መሸሻ ገብሩ አሉበት በመባል ይታሰሱ ስለነበር ወንድማቸውን ከአደጋ ለማዳን ሲሞክሩ ወይዘሮ ስንዱ በድጋሚ በፋሺስቶች እጅ ወደቁ። በወቅቱ ግራዚያኒ ይኖርበት የነበረው የገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ውስጥ ታሰሩ። ቀጥሎም ወደ አስመራ፣ ከዚያ ወደ ምጽዋ ተወሰዱ። ከምጽዋ ወደብ ሦስት መቶ ወንዶችና ስምንት ሴቶች (እማሆይ ጽጌ ማርያምን ጭምር) ሆነው በመርከብ ‹‹አዚናራ›› ወደተባለች የኢጣሊያኖች እስር ቤት ተወስደው ዘጠኝ ወራት ታሰሩ።

ከእስር በኋላም ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ በእንደዚህ ያለ ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም፤ ማስፈራሪያው ሳይበግራቸው አርበኞችን በግጥምና ወኔ ቀስቃሽ ጽሑፎች በማበረታታት፣ መረጃ በማቀበል፣ መሣሪያ በማዳረስ የጀግንነት ተግባር ፈጽመዋል።

ከድል በኋላ ወይዘሮ ስንዱ ለሁለት ዓመታት ደሴ ከተማ የሚገኘው የወይዘሮ ስኂን ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ በመሆን፣ በኋላም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰውም የእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሰ መምህርነት፣ ከዚያም የመጀመሪያዋ ሴት ርዕሰ መምህር ሆነው አገልግለዋል። በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት፤ ‹‹ኮከብ ያለው ያበራል ገና››፣ ‹‹የየካቲት ቀኖች››፣ ‹‹የኑሮ ስህተት›› የሚሉ ትያትሮችን ሠርተው አቅርበዋል።

ወይዘሮ ስንዱ ከ1948 ዓ.ም እስከ 1952 ዓ.ም ድረስ የመጀመሪያዋ የሴት የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባልና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ምክትል ሊቀ መንበር ሆነው አገልግለዋል። በዚህ ምክር ቤት አባል በነበሩበት ጊዜ ብቸኛዋ ሴት ከመሆናቸውም ባሻገር የሴቶች እኩልነት በማይከበርበት ጊዜ እና ‹‹የወንድ ዓለም›› በገነነበት የታሪክ ምዕራፍ የሴቶችን ሰብዓዊ መብት ለማስከበርና እኩልነትን በሕግ ለማስተማመን ብዙ የታገሉ ሴት ነበሩ።



ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ ደስታ

### ስንዱ ገብሩ ከተሳተፉባቸው ጥቂቶችን እንጥቀስ

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማኅበር ፕሬዚዳንት፣ የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ዋና ፀሐፊነትና አስተዳዳሪነት፣ በምዕራብ ጀርመን ለሦስት ዓመት የትምህርት አታሼ ሆነው አገልግለዋል።

**ከመጽሐፎቻቸው ደግሞ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።**

ኮከብህ ያውና ያበራል ገና፣ በግራዚያኒ ጊዜ የየካቲት ቀኖች (1947 ዓ.ም)፣ የታደለች ህልም (1948 ዓ.ም)፣ ርእስ የሌለው ትዳር (1948 ዓ.ም)፣ የኔሮ ስህተት (1948 ዓ.ም)፣ ከማይጨው መልስ (1949 ዓ.ም)፣ ፊታውራሪ ረታ አዳሙ (1949 ዓ.ም) እና የመሳሰሉት ሌሎች ጽሑፎቻቸው ይጠቀሳሉ።

የመጀመሪያዋ የሴት ፓርላማ አባል፣ የሴት የሰብዓዊ መብት ተሟጋች፣ ጀግና እና ፀረ ፋሺስት አርበኛ፣ ፀሐፊ ተውኔት፣ የመጽሐፍ ደራሲ፣ እና የመጀመሪያዋ የሴት ዲፕሎማት ስንዱ ገብሩ (የክቡር ዶክተር) ሚያዝያ 12 ቀን 2001 ዓ.ም በተወለዱ በ93 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ተለይተዋል። ሥርዓተ ቀብራቸውም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የክብር ዶክትሬት ሰጥቷቸዋል።



## የኮሪያ ዘማች

ዋስልኝ አየለ

**ሄዶ ከኮሪያ ዘማች ሲመለስ**
**ያወሳል ናፍቆቱን በክራሩ ድምጽ**

ብሏል ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ)። በዚህ ሳምንት ከምናስታውሳቸው የታሪክ ክስተቶች አንዱ የኮሪያ ዘማች ታሪክ ነው። የኮሪያ ዘማች ትውስታ ባለክራሩን የሙዚቃ አርበኛ ካሳ ተሰማን አስከትሎ ወደ ኮሪያ የሄደው የኢትዮጵያ አርበኞች ታሪክ ነው።

ክስተቱ ከሚያዚያ 8 ቀን ጀምሮ በ1943 ዓ.ም በዚህ ሳምንት ነው። 2 ሺህ 168 ወታደር ያሰለፈው የኢትዮጵያ የክቡር ዘበኛ ሠራዊት፣ ቃኘው የሻለቃ ጦር ወደ ኮርያ ዘመተ። ከዘማቾቹ መካከል አንዱ የነበረው ‹‹የክራሩ ጌታ›› 50 አለቃ ካሣ ተሰማ ይገኝበታል። ‹‹እልም አለ ባቡሩ›› በሚለው ዘፈኑም ክስተቱን ለታሪክ አስቀምጦታል።

የመጀመሪያው ዙር የኮሪያ ዘማቾች አንድ ሺህ 153 ሲሆኑ ቀኑ ግን በትክክል አልተገለጸም። አብዛኞቹ መረጃዎች የሚያሳዩት በመጋቢት ወር መጨረሻ አካባቢ መሆኑን ነው። የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከአራት ዓመት በፊት በሰራው ዘገባ መጋቢት 30 የሚል አለው። ምናልባት እሱ የመጀመሪያው ከሆነ የሚያዚያ ስምንትና ዘጠኝ አካባቢ ያለው ሁለተኛው ዙር ይሆናል ማለት ነው። ያም ሆነ ይህ የኮሪያ ዘማቾች በዚህ ሳምንት ይታወሳል ማለት ነው።

የኮሪያ ዘማች እና ከኮሪያ ዘማቾች ማህበር መሥራች አንዱ የሆኑት የማህበሩ ፕሬዚደንት ኮሎኔል መለሰ ተሰማ በተመሳሳይ ከዘማቾች አንዱ የሆኑት አስር አለቃ ዘነበወርቅ በላይነህ የኮሪያ ዘማቾች 60ኛ ዓመት ሲከበር ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገው ነበር።

ዘማቾቹ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ዘመቻው በአምስት ዙር ነበር። በአጠቃላይ ከስድስት ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የዘመቱ ሲሆን 122 የሚሆኑት ተሰውተዋል። ከኢትዮጵያ ወታደሮች አንድም የተማረከ አልነበረም፤ ‹‹ሬሳ እንኳን አልተማረከብንም›› ይላሉ ዘማቾቹ።

በ2005 ዓ.ም የኮሪያ ጦርነት 60ኛ ዓመት ሲዘከር ቢቢሲ ዓለም አቀፍ ‹‹ኢትዮጵያዊው ጀግና በኮሪያ ጦርነት›› በሚል ርዕስ የኮሪያ ዘማች ስለነበሩት ሌተናል ጄነራል ማሞ ሀብተወልድ ሰፊ ሐተታ አስነብቧል። በዚህም የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት ለዓለም አሳውቋል። የቢቢሲ ዓለም አቀፍ ሐተታ የመግቢያው ጽሑፍ ደመቅ (Bold) ተደርጎ እንዲህ ተጽፏል።

‹‹ከ60 ዓመታት በፊት፤ ኢትዮጵያ ጦርነት ላይ ነበረች። ጦርነቱ አፍሪካ ውስጥ እንዳይመስላችሁ! ይልቁንም በሺዎች የሚቆጠር ማይል ርቀት ላይ ኮሪያ ውስጥ ነው...›› እያለ ይቀጥላል።

ቢቢሲ በዚያው ሐተታው እንደገለጸው፤ ኢትዮጵያውያን በኮሪያ 253 ውጊያዎችን (battles) አድርገዋል። ‹‹በጦር ሜዳ እጅ አንሰጥም!›› የሚል መሪ ቃል ነበራቸው። መሪ ቃላቸውንም በተግባር አሳይተዋል።

እነሆ ኢትዮጵያም በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለምም ሰላም በማስከበር እንድትታወቅ አደረጋት። እነዚህ የኮሪያ ዘማች ጀግኖችም ሲታወሱ ይኖራሉ።

# የዝነኞች ገጽ

# ጥበብ የወለደቻቸው ጥበበኛ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ከዚያም ይልና ታሪኩን በአለ ይጀምራል። አለ ስማቸው ነው። የሰዓሊ አለቃ ኀሩይ የልጅ ልጅ፤ አለ ፈለገሰላም፤ ስራዎቻቸው ደግሞ አለ ፈለገጥበብ ያስብላቸዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም። በኢትዮጵያ የስዕል ታሪክ ውስጥ የእሳቸውን ያህል አሻራቸውን ማሳረፍ የቻሉ ምናልባትም አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ይኖሩ ይሆናል። እንደሳቸው ግን ከአፍላ ወጣትነት እስከ እርጅናቸው ዘመን ድረስ ለስዕል ጥበብ እራሳቸውን የሰጡ ሰዎች ፈልጎ ማግኘት ከባድ ነው። ያምሆኖ የእኚህ ታላቅ የጥበብ ሰው ስራ በታሪካቸው ማህደር በአግባቡ ተሰድሮ ሳይቀመጥ ቀርቷል።

ሐምሌ 24 ቀን 1915 ዓ.ም በድሮዋ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት በፍቼ ገነት ከተማ ውስጥ ነው የተወለዱት። አባታቸው ፈለገሰላም ኀሩይ በስዕል ጥበብ የተካኑ ሰው ነበሩ። አያቱን ሰዓሊ አለቃ ኀሩይን ጨምሮ በቤተሰቡ ውስጥ አራት ያህል ሰዓሊያን የነበሩ ሲሆን ይህቺ ታላቅ ጥበብ በልዩነት በአለ ፈለገሰላም ላይ ጎልታ ታይታለች። ከሰማይ ሁለቱንም ክንፏን ዘርግታ ያረፈችባቸውም ትመስላለች። ጥበቡ ውስጥ የተወለዱ ጥበብ ናቸው ማለት ይቀላል። አሳዳጊያቸውና አያታቸው የሆኑት አለቃ ኀሩይ በልጅነታቸው ከሥዕል ይልቅ ወደ ቤተክህነት ትምህርት እንዲያተኩሩ ይገፋፏቸው እንደነበር ይናገራሉ። በዚህም በልጅነታቸው አለቃ ጥበቡ ከተባሉ መምህር ስር ቅኔ እየዘረፉ፣ ዜማ እየተቃኙ አድገዋል። በልጅነታቸውም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የድቁና ማዕረጋቸውን ተቀብለዋል።

ከፍቼ ከተማ አህዱ ብሎ የሚጀምረው ደማቁ ታሪካቸውን ማየት ለቻለ በኢትዮጵያ የጥበብ ሰማየ ሰማያት ላይ ግሩም የቀለማት ህብርን ሰርቶ ቁጭ ብሏል። የፋሽስት ጣሊያን መንግስት ኢትዮጵያን ለቆ በወጣበት በ1934 ዓ.ም አለ ፈለገሰላም ከፊቼ ተነስተው የአጎታቸውን እጅ በመያዝ ተከትለው አዲስ አበባ ገቡ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውንም 1940 ዓ.ም አጠናቀቁ። 1943 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ቴክኒክ ትምህርት ቤት ገብተው በጥሩ ውጤት ተመረቁ።

ከዚያ በኋላ ከአፄ ኃይለስላሴ በተቸራቸው ነጻ የትምህርት እድል ወደ አሜሪካ አቀኑ። በአሜሪካን ቺካጎ የስነጥበብ ተቋም ውስጥ በመግባት በ1946 ዓ.ም በፋይን አርትስ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ማግኘት ቻሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ በዘመናዊ የስዕል ትምህርት የተመረቁ የመጀመሪያው ሰውም እሳቸው ነበሩ። በ1947 ዓ.ም ተመልሰው ወደአገራቸው በመምጣት በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ መስራት ጀመሩ። በዚያም የተለያዩ የህጻናት መማሪያ መጽሀፍትን እያዘጋጁ ቆዩ። አለ ፈለገሰላም ህጻናትን እጅግ በጣም አብዝተው ይወዱ ስለነበር ከአሜሪካን አገር ቋጥረው ባመጧት ትንሽ ገንዘብ አዳራሽ ተከራይተው ህጻናቱን እየሰበሰቡ ስነ-ስዕልና ልዩ ልዩ የቀለም ትምህርቶችን ያስተምሩ ነበር። ጥሩ የእውቀት ገበሬ ናቸውና በህጻናቱ ለምለም አዕምሮ ላይ ጥበብን ዘሩበት። የዘሩትም በቀለ፤ በውብ ማሳ ላይ ውብ አዝመራ ታየ። በብዙ ጥረት፣ በብዙ ትጋት እየተንከባከቡና እየኮተኮቱ የዚያችን አዳራሽ አድማስ በማስፋት የስነ-ስዕል ትምህርት ቤት ለማድረግ በቁ። በአሁኑ ሰዓትም ትምህርት ቤቱ በስማቸው ተሰይሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር ይገኛል። እንጦጦን የማልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ዘመናዊ የአውደ-ርዕይ ማሳያ በትምህርት ቤቱ እስከመገንባት ደርሷል።

አለ ፈለገሰላም በሚሰሯቸው የስዕል ስራዎች ስማቸው እስከ ቤተመንግሥት ድረስ የናኘ ነበር። ከእሳቸው በፊትም ሆነ በጊዜው ሌሎቹ ሰዓሊያን የሚታወቁት በትውፊታዊ ስዕሎች ሲሆን አለ ፈለገ ሰላም ግን የዘመናዊ ስዕልን ዙፋን በብቸኝነት የተቆጣጠሩ ታላቅ የጥበብ ሰው ናቸው። የቀደምቶቻቸውን የስዕል ጥበብ ዱካ ተከትለው ቀለማትን ከጥበብ ጋር በማዋደድ ከሰሯቸው ድንቅ ስራዎች የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል፣ የጎፋ ገብርኤልን ጨምሮ በመርካቶ የሚገኙትን የቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል እና የቅዱስ ራጉኤልን ቤተክርስቲያን መለኮታዊ ጥበብ ባረፈበት እጃቸው ብሩሹን እያነሱ ዘመናት የማይሽሯቸውን ስራዎች ማስቀመጥ ችለዋል። ሌላው በቤተክርስቲያን ውስጥ ከሰሯቸው ስራዎች ደግሞ የናዝሬት ደብረጸሐይ ቅድስት ማርያም ካቴድራል እንዲሁም በቁልቢ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የጥበብ አሻራቸውን አኑረዋል። በዚህ ሳይገቱም ስራቸውን እስከ ባህር ማዶ በማስፋት በአሜሪካን አገር በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘውን የመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያንን የሥዕል ስራ ግሩም በሆነ መልኩ ሰርተውታል። የሚገርመው ነገር ደግሞ ሁሉንም በሚሰሩበት ወቅት ወጣ ባለመልኩ ሸራውን ግርግዳው ላይ ከለጠፉት በኋላ ነበር።

የዘውዳዊ ስርዓት አክትሞ የደርግ መንግስት ሲመጣ ከነበሩበት የስዕል ትምህርት ቤት 1967 ዓ.ም ከዳይሬክተርነት በፈቃዳቸው ተነሱ። ከዚህ በኋላ በመንግሥት ተሹመው በባህል ሚኒስትር ለአምስት ዓመታት የቅርስ ጥገና ክፍል ሲሰሩ ቆዩ። ነገር ግን ወደ መጨረሻ አካባቢ ከመንግስት ጋር ኮከባቸው አልገጥም አለና እሰጣገባ ውስጥ እየገቡ መቃቃር ጀመሩ። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ እየሸፈጡ መንግስትን አስቸገሩት። እሳቸውም የመንግስት ነገረ ስራ ሁሉ አልጥም አላቸውና "እንካችሁ ወንበሩን" በማለት ጥለው ሄዱ። ከዚህ ኋላ ግን ከሁሉም ቦታ ተገለው ቀሩ። የደርግ መንግስት አልፎ የኢህአዴግ መንግስት ዙፋኑን ሲረከብ እሳቸውም በ80ዎቹ ካሉበት በባትሪ ተፈልገው፣ ያቋቋሙትን የስዕል ትምህርት ቤት ዳግም እንዲይዙት ተደረገ። ከዚህ በኋላ ሰዓሊው አለ በጊዜው በግንባታ ላይ ከነበረው የናዝሬት ደብረሰላም ቅድስት ማርያም ካቴደራል አስተዳደር ጋር ስምምነት በማድረግ ወደ አዳማ አቀኑ። ከተማዋም የተለየ የፍቅር ስሜትን ስለዘራችባቸው ከዚያው ሳይወጡ ቤትና መሬት ገዝተው እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ከዚያው ከአዳማ ቆዩ። ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ ወዲያ ግን አቅማቸው ስለደከመ የሚሰሩባቸውን መሳሪያዎች ለተለያዩ ሰዎች በስጦታ መልክ ሰጡ። የሰጡት መሳሪያዎቹን ብቻ ሳይሆን ታላቅ የስዕል ጥበብን ከታላቅ አደራ ጋር ነበር።

አለ ፈለገሰላም ጥበብ በትውልድ መካከል እንዳትመክን ቤተሰቦቻቸው ያስተማሯቸውን ትውልድ አሻጋሪነት እሳቸውም በተለያዩ ጊዜያት የእሳቸው ለም መሬትና ተማሪዎቻቸው በነበሩት ላይ ዘርተውታል። እሳቸውም ያላገኟትን ሌላኛዋንም የጥበብ በር እንዲያገኙ ጭምር ይመክሯቸው ነበር። የነበሯቸውን የእነ ሚካኤል አንጀሎን፣ ሊዮናርዶ ዳቪንቺን እንዲሁም የሌሎችንም የቅርጻ ቅርጽ መጽሐፍቶቻቸውን እየገለጡ ያሳዩና ስራዎቹንም ለማሻሻል የሚረዱ ምክረ ሀሳቦችን ይሰጧቸው እንደነበረም ከጠቢቡ ሰዓሊ እግር ስር ቁጭ ብለው ጥበብን የተማሩት በአንደበታቸው ይመሰክራሉ። አለ ፈለገ ሰላም የሰሯቸውን ስራቸው ከአገር ውጭ በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች እየዞሩ አሳይተዋል። በ1953 ዓ.ም የኢትዮጵያ ወቅታዊ ጥበብ በሚል በሩስያ ሞስኮ እንዲሁም በ1960 ዓ.ም በካናዳ ሞንቴሪያል የሥዕል ዐውደ-ርዕይ ማሳየት ችለዋል።

## አለ የሞት ፍርድ ተበየነባቸው

ጊዜው ጣሊያን ኢትዮጵያን የወረረበት ወቅት ነበር። ታዳጊው አለና ጓደኛቸው ተያይዘው ከቤት ይወጣሉ። ከሰፈራቸው አቅራቢያ የሚጫወቱ ልጆችን አገኙና እነርሱም ተቀላቀሉ። አለ በእጃቸው አንድ ዱላ ይዘው ነበር። ይህንን የተመለከተ አንድ የጣሊያን አሽከር ቀልቡ ዱላዋ ላይ ያርፍና 'ዱላውን አምጣው' ሲል በትዕዛዝ ጠየቃቸው። በዚህ ጊዜ የአለ ጓደኛ ፈጠን ብሎ 'ለምን ይሰጥሃል በራስህ ዱላ ተጫወት' ይለዋል። አሽከሩ ይህን ሲሰማም ደፈርከኝ በሚል ንዴት በያዘው ዱላ ጭንቅላቱን መታው። አለም ከልጁ የባሰ ነደው፣ በዱላው የአሽከሩን አናት ብለው ይዘርሩትና በድንጋጤ ከጓደኛቸው ጋር ተያይዘው እልም ይላሉ። በኋላ ነገሩን ሲሰሙም አሽከሩ ወዲያውኑ ጭጭ ብሏል። በማግስቱም ወታደሮች እቤት ድረስ መጥተው አንጠልጥለው ወሰዷቸው። አራት ቀንም ያለ እህልና ውሃ ከእስር ቤት ከቆዩ በኋላ የሞት ፍርድ ተፈርዶብሃል ተባሉ። ከሌሎች እስረኞችም ጋር ይዘዋቸው ወደ ገደል አፋፍ ከወሰዷቸው በኋላ የሚቀበሩበትን መቃብር እራሳቸው እንዲቆፍሩም ታዘዙ። አለ ፈለገሰላምም መሞቴ እንደሆን አይቀር ስለዚህ አሉና፤ ዙሪያ ገባቸውን ቃኘት ቃኘት ሲያደርጉ ከዙሪያው ገደል ተመለከቱ። እንደገና ዞር ቢሉ አንደኛው ፖሊስ ትንሽ እራቅ ብሎ ሲጋራውን ለኩሷል። አካፋውንም ጥለው እግሬ አውጪኝ ሲሉ፤ እግራቸው እንደመራቻቸው ቁልቁል ወደገደሉ ፈረጠጡ። ወታደሮቹም ይተኩሳሉ፤ አለ ግን የባሩዱን ድምጽ እየሰሙም በድንጋጤ በየት ኩል አድርገው ወዴት እንደሄዱ አያውቁትም፣ ብቻ ሁሉም ነገር በደመነብስ ከሞት ሽሽት የሚደረግ ትግል ነበር። ከገደሉ ውስጥ ገቡና በቅጠል ተሸፋፍነው ድምጻቸውን አጠፉ። ወታደሮቹም ቢያዳምጡ ምንም ድምጽ የለም። በዚህ ጊዜ ከጥይቱ ቢያመልጥም እንኳን ከገደሉ ተርፎ ሊወጣ አይችልም በማለት ትተው ሄዱ። ቤተሰቦቻቸውም አለ ሞቷል ብለው ለቅሶ ተቀመጡ በመጨረሻ ግን አወቁ። ይህቺ አጋጣሚም እኚህ ትልቅ ሰው ዳግም የተወለዱባትና ለኢትዮጵያ የስዕል ጥበብ ወሳኟ ሰዓት ነበረች።

ታላቁ የጥበብ ሰው አለ ፈለገሰላም የሰሩት ብዙ ቢሆንም ምስጋናና ሽልማቱን ያገኙት ግን በጥቂቱ ነው ለማለት ያስደፍራል። ሆኖም ግን ካገኟቸው እውቅናና ሽልማቶች በአሜሪካ፣ በጀርመን፣ በህንድ፣ በሶቪየት ኅብረት፣ በቼኮዝላቫኪያ፣ በግሪክና በዩጎዝላቪያ የሥዕል ዐውደ-ርዕዮዎችን በማሳየት የተለያዩ ሽልማቶችም አግኝተዋል። የኢትዮጵያ ሚሊንየም በሚከበርበት ወቅትም ሲድ (SEED) በተባለ አሜሪካን አገር ያለ ተቋም የሥዕል ጥበብን ለማስተማር ላደረጉት ጉልህ አስተዋጽኦ ሽልማት አበርክቶላቸዋል።

በመጨረሻ አቅማቸው እየደከመ እርጅናቸውም እየበረታ መጣ። እስትንፋሳቸውም ከዳቸውና በወርሃ ሐምሌ 2008 ዓ.ም ነብሳቸው ከስጋቸው ተለየች። ሁሉም ከመቃብር ወዲያ ማዶ ሆኑ። ስማቸው ግን ለዘለዓለሙ ከመቃብር በላይ ናት። ይህቺ ባለሁለት ፊደላት ትንሿ ስም 'አለ' እኔም እላለሁ፤ እምቅ ቅኔ ሆና እኚህን ታላቅ ሰው ተሸክማ ኖረች። ከሞት በኋላም ታሪካቸውን ተሸክማ እነሆ ከመቃብር በላይ ገዝፋ በደማቁ እያበራች በትውልዱ ሁሉ ትኖራለች።



**አለ ፈለገሰላም በሚሰሯቸው የስዕል ስራዎች ስማቸው እስከ ቤተመንግሥት ድረስ የናኘ ነበር። ከእሳቸው በፊትም ሆነ በጊዜው ሌሎቹ ሰዓሊያን የሚታወቁት በትውፊታዊ ስዕሎች ሲሆን አለ ፈለገ ሰላም ግን የዘመናዊ ስዕልን ዙፋን በብቸኝነት የተቆጣጠሩ ታላቅ የጥበብ ሰው ናቸው**

# ዓለም አቀፍ

## በደቡብ አፍሪካ በተከፈተ ተኩስ 10 የአንድ ቤተሰብ አባላት ተገደሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በደቡብ አፍሪካ ቤታቸው ላይ ጥቃት የተፈጸመባቸው የአንድ ቤተሰብ 10 አባላት መገደላቸውን ፖሊስ ገልጿል።

ፒተርማሪትዝበርግ ከተሰኘው ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ትናንት አርብ በደረሰባቸው ጥቃት ከተገደሉት የቤተሰብ አባላት ሰባቱ ሴቶች መሆናቸውን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

የደቡብ አፍሪካ የፖሊስ ሚኒስትር ቤሄኪ ሴሌ አንድ ተጠርጣሪ በፖሊስ ተተኩሶበት መገደሉን እንዲሁም ሌሎች ሁለት ሰዎች መታሰራቸውንና አንድ ተጠርጣሪ እየተፈለገ እንደሚገኝ ገልጸዋል። ግድያው የተፈጸመበት ምክንያት እስካሁን አልታወቀም።

ደቡብ አፍሪካ በከፍተኛ ቁጥር ግድያ ከሚፈጸምባቸው አገራት አንዷ ናት።

ጥቃቱ በተፈጸመበት ስፍራ አቅራቢያ የሚኖሩ ሰዎች የተኩስ ድምጽ መስማታቸውን ተከትሎ ለፖሊስ በማሳወቃቸው ጉዳዩ ተደርሶበታል።

የፖሊስ ሚኒስትሩ ከጥቃቱ ሰለባዎች መካከል የ13 ዓመት ልጅ እንደሚገኝ ገልጸው ወንጀሉ የተፈጸመበት ቦታ የሚያሳቅቅ ነው ብለዋል።

ሚኒስትሩ በምስራቃዊ የደቡብ አፍሪካ ክፍል ካውዙሉናታላ ግዛት በምትገኘው ኢምባሊ የተሰኘች አነስተኛ ከተማ የተፈጸመውን ጥቃት አስመልክቶ ለጋዜጠኞች ሲናገሩ ሁለት ሰው ታስሯል፣ አንዱ ተጎድቷል፣ አንደኛው አምልጧል። ሶስት መሳሪያዎችም ተገኝተዋል።

ከጥቃቱ በኋላ አንድ ህጻን ልጅ ወደ ሆስፒታል ተወስዷል።

ጥቃቱን የፈጸሙት ታጣቂዎች የፖሊስ አባላት መስለው ወደ ቤት ውስጥ መግባት እንደቻሉ የአገር



ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል።

ፖሊስ ተጠርጣሪዎቹ ከተሸሸጉበት የባህል ህክምና መስጫ ቦታ መያዛቸውን የገለጸ ሲሆን የተገደለው ተጠርጣሪ በፖሊስ ለረጅም ጊዜ ሲፈለግ የነበረ እንደሆነ አስታውቋል።

ጥቃቱ የተፈጸመበት አካባቢ በደቡብ አፍሪካ ተደጋጋሚ ግድያ ከሚፈጸምባቸውና መፍትሄ ሊያገኙ ካልቻሉ አካባቢዎች አንዱ ነው።

በደቡብ አፍሪካ በዚህ ሳምንት የጅምላ ግድያ ሲፈጸም ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ነው።

ባለፈው ሀሙስ በምስራቃዊ የአገሪቱ ክፍል በምትገኘው የወደብ ከተማ አራት ሰዎች ተኩስ ተከፍቶባቸው ተገድለዋል።

በጥር ወርም በዚያው ደቡብ አፍሪካ በልደት ድግስ ላይ ስምንት ሰዎች የተገደሉ ሲሆን ባለፈው ዓመት ደግሞ በምሽት መዝናኛ ቤት ውስጥ በተፈጸመ ጥቃት 15 ሰዎች ተገድለዋል።



## የውጭ አገራት ዜጎቻቸውን ከካርቱም ለማስወጣት እየተዘጋጁ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሳምንት የደፈነው የሱዳን ጦርነት ተፋፍሞ ከመቀጠሉ ጋር ተያይዞ የውጭ አገራት ዜጎቻቸውን ከመዲናዋ ካርቱም ለማስወጣት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የአውሮፓ ህብረት ዜጎቹን ከካርቱም ለማስወጣት እቅድ መንደፉን አስታውቋል።

አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን እንዳሉ የህብረቱን አባል አገራት ዜጎችም ለማስወጣት የተለያዩ አማራጮችን እያጤኑ እንደሚገኙም ነው።

በካርቱም ወደ 1 ሺህ 500 የሚጠጉ የህብረቱ አባል አገራት ዜጎች ይገኛሉ። ሰባት የአውሮፓ ህብረት አባል አገራት በሱዳን ተልዕኮ አላቸው።

የጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና ባየርቦክ ዜጎችን ለማስወጣት የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ መድረስ ቀዳሚ ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል።

ግጭቱ ከተከሰተበት ሚያዝያ 7፣ 2015 ዓ.ም ጀምሮ የካርቱም ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እንደተዘጋ ይገኛል።

አሜሪካ የዲፕሎማቲክ ሰራተኞች ካርቱምን ለቀው እንዲወጡ ለማድረግ ውሳኔ ላይ እንዳልደረሰች ገልጻለች። ባለስልጣናቱ ከኤምባሲው ሰራተኞች ውጭ ያሉ ሌሎች የአሜሪካ ዜጎች ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ በራሳቸው እንዲዘጋጁ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ባለስልጣናቱ ይህንን ይበሉ እንጂ አሜሪካ ዜጎቿን ለማስወጣት በዝግጅት ላይ መሆኑን ዘገባዎች አሳይተዋል።

የአሜሪካ ጦር የኤምባሲውን ሰራተኞች ከካርቱም ለማስወጣት እየተዘጋጀ መሆኑንም ተዘግቧል።

የአሜሪካ ወታደሮች በጂቡቲ ወደሚገኝ ወታደራዊ ካምፕ እየተወሰዱ እንደሆነም የአገሪቱ ሚዲያዎች ዘግበዋል።

አርብ እለት የአሜሪካ የጦር ሰራዊት ጀነራል ማርክ ሚሌይ ከጦር አዛዡ ጄነራል አብደል ፈታህ አል ቡርሃን ጋር በሱዳን ስላሉት አሜሪካውያን ደህንነት ተወያይተዋል። ፔንታጎን በጉዳዩ ላይ ምንም አይነት ዝርዝር መረጃ አልሰጠም።

ደቡብ ኮሪያ በበኩሏ ዜጎቿን ከሱዳን ለማስወጣት ወታደራዊ አውሮፕላን እንደምትልክ ማስታወቋን ዮንሃፕ የተሰኘው የዜና አገልግሎት ዘግቧል።

በርካታ ወታደሮች እና የህክምና ባለሙያዎችን የያዘው አውሮፕላን ወደ ሱዳን እንደሚያመራም ሚዲያው የጸጥታ ምንጮችን ጠቅሶ ዘግቧል።

ጃፓን መከላከያ ሰራዊቷ 60 የሚጠጉ ዜጎቿን ከሱዳን እንዴት ማስወጣት እንደሚቻል እያጠነ መሆኑንና ወታደራዊ አውሮፕላንም በተጠባባቂነት ተይዟል ብላለች።

የታንዛንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስተርጎሜና ታክስ ለፓርላማቸው እንደተናገሩት መንግሥታቸው 210 ዜጎቿን የሚያስወጣበት ሁኔታን እየገመገመ ነው።


### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም ፡- ዢአኦ ቢ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ. 04 የቤት ቁጥር. አዲስ, ሰበታ, ፉሪ, ኦሮሚያ ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/13928/2015<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 04/07/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡<br>B&B | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡ |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 16 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ፐልፐ እና/ወይም ወረቀት ማምረት (ምድብ 16) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOL LXXXII NO 225 15/8/2015 (23/4/2023)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም ፡- ዢአኦ ቢ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ. 04 የቤት ቁጥር. አዲስ, ሰበታ, ፉሪ, ኦሮሚያ ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/13938/2015<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 04/07/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡<br>Yoursun | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡ |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 16 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ፐልፐ እና/ወይም ወረቀት ማምረት (ምድብ 16) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOL LXXXII NO 225 15/8/2015 (23/4/2023)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም ፡- Mss XIAOHUI BAI<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 04 የቤት ቁ. አዲስ, ፉሪ ሰበታ, ኦሮሚያ ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/13931/2015<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 04/07/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡<br>WaWa | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡ |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 16 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ፐልፐ እና ወረቀት ማምረት (ምድብ 16) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOL LXXXII NO 225 15/8/2015 (23/4/2023)

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ


| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም ፡- MSS XIAOHUI BAI<br>የአመልካች አድራሻ፡- ፉሪ ሰበታ ወረዳ 04 የቤ/ቁ, አዲስ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/13934/2015<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 04/07/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡<br>Goodbaby | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡ |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 16 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ፐልፐ እና ወረቀት ማምረት (ምድብ 16) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOL LXXXII NO 225 15/8/2015 (23/4/2023)

# ስፖርት



# የክፍለ ዘመኑ አንጸባራቂ ኮኮብ

**አስማየሁ ግዛው**

ውድድር ካቆመ እነሆ ስምንት ዓመታት ተቆጥረዋል፤ ዛሬም ድረስ ግን የትልልቅ መገናኛ ብዙሃን ርእስ ነው። ባለፈው ማክሰኞ የ50ኛ ዓመት ልደት ሻማውን መለኮሱን ተከትሎም መላው ዓለም የእንኳን አደረሰህ መልእክቱን አዥጎድጉዶለታል። ዓለም አቀፍ ጋዜጦችና መጽሄቶችም ኃይሌ ገብረስላሴን ‹‹የምንጊዜውም የዓለም ምርጡ አትሌት ነው›› በሚል ከአእምሮ በላይ የሆነ ድንቅ ብቃቱን የሚመሰክሩ ፅሁፎችን ለአንባቢ አድርሰዋል። በእርግጥም ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ በአትሌቲክስ ስፖርት ታሪክ የታየ የምንጊዜም ምርጡ አትሌት ነው። ይህም ዓለም በአንድ ድምፅ የሚስማማበት ሃቅ ነው።

አትሌቲክስ ዊክሊ የተሰኘው የአትሌቲክስ መጽሄት ኃይሌ ውድድር ማቆሙን ተከትሎ ለአንባቢዎቹ ባቀረበው የረጅም ርቀት ሯጭ ምርጫ፤ 45ነጥብ6 በመቶ ድምጽ በማግኘት የመጀመርያውን ስፈራ መያዝ ችሏል። ከዚያ ምርጫ በኋላ እንግሊዛዊው ሞ ፋራህ ብዙ የዓለም እና የኦሊምፒክ ስኬቶችን አሸንፏል። ኬንያዊው ኢሉድ ኪፕቾጌም በሁለት የኦሊምፒክ መድረኮች፣ በትልልቅ የከተማ ማራቶኖች የዓለም ክብረወሰንን ከሁለት ሰዓት በታች በመግባት የማስመዝገብ የሙከራ በማድረግ ዓለምን ህዝብ በአግራሞት እጁን አፉ ላይ አስጭኗል። ነገር ግን አንዳቸውም ከኃይሌ የሚበልጥ ታሪክ መጻፍ አልቻሉም።





አገር ወዳዱ፣ ጨዋታ አዋቂው፣ የአገር ሽማግሌው፣ ስኬታማው የንግድ ሰው፣ ስራ ፈጣሪው፣ የጽናት ተምሳሌቱ፣ በጎ አድራጊው፣ ... ቢሰነዝሩ የማይደርሱበት ከፍታ ላይ ይገኛል። የሰራቸው አስገራሚና ታላላቅ ገድሎች የክፍለ ዘመኑን ታላቅ አትሌትነት ስፍራን እንደተቆናጠጠ እንዲቆይ አስችሎታል። ኃይሌ የተወለደው በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው ሳምንት እአአ ሚያዝያ 18/1973 በአርሲ ዞን አሰላ ነበር። ከትምህርት ቤት የሚነሳው የሩጫ ህይወቱ እአአ በ1992 በሴኡል በተካሄደው የዓለም ታዳጊዎች ቻምፒዮና የ5 ሺ እና 10ሺ ሜትር ወርቅ በማሸነፍ ለመጀመርያ ጊዜ ስሙን በዓለም አቀፍ የውድድር መድረክ ማስመዝገብ አስችሎታል። በዚህ ወቅት በተለይ ትኩረትን ስቦ በነበረው የ10ሺ ሜትር ውድድር ሲሆን፤ በተቀናቃኙ ኬንያዊ አትሌት ጆሴፍ ማቹካ በቡጢ ተመትቶ የመጨረሻውን መስመር ማለፉ ነበር።

ይኸው ሁኔታ ኃይሌን ያስፈነጠረው ወደ መጨረሻው መስመር ብቻም ሳይሆን በአትሌቲክስ ስፖርት ታላቅ ወደሆነው ውድድር የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ይመስላል። ምክንያቱም በቀጣዩ ዓመት በጀርመን ስቱትጋርት በ10ሺ ሜትር የወርቅ በ5ሺ ሜትር ደግሞ የብር ሜዳሊያ ያገኘበት በመሆኑ ነው። ከዚያ በኋላ ከስኬት ጫፍ የወጣውን ኃይሌን የሚስተካከል አትሌት ማግኘት አልተቻለም። እአአ ከ1993 እስከ 2003 በተካሄዱ ቻምፒዮናዎችም 4 የወርቅ፣ 2 የብር እና 1 የነሃስ በጥቅሉ 7 ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ የአትሌቲክስ ቤተሰቡን አጀብ አሰኝቷል።

የዓለም አትሌቲክስም በዚሁ ምክንያት በ1990ዎቹ የእሱን ያህል በተደራራቢ ክብር የተንቆጠቆጠ አትሌት የለም ሲል ስሙን በቀዳሚነት ያሰፍራል። ከወራት በኋላ በቡዳፔስት በሚካሄደው የዓለም ቻምፒዮና የሚከበረውን የውድድሩን 40ኛ ዓመት አስመልክቶም ምርጥ ክስተቶች በሚል ለዓለም የአትሌቲክስ ቤተሰብ ለምርጫ ከቀረቡ አትሌቶች መካከል አንዱ ሆኗል። ጀግናው አትሌት በኦሊምፒክ መድረክም አስደናቂ ገድል ያጻፈ ሲሆን፤ ለማሸነፍ በሚያደርገው ጥረት እና ብርታት የተመሰረተ (endurance) የሚል ፊልምም ተሰርቶለታል። የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮናን ጨምሮ በጎዳና ላይ ሩጫም የስፖርት ቤተሰቡን አጀብ ያሰኘ ተሳትፎና ስኬት ነበረው። በዚህም ለንደን፣ በርሊን፣ አምስተርዳም፣ ፎኮካ፣ ዱባይ፣ ኒውዮርክ እና ቶኪዮ ማራቶኖችን ለተከታታይ ዓመታት፣ በየዓመቱ ሁለትና ከዚያ በላይ ማራቶን በመሮጥ ለማመን የሚከብድ አስደማሚ ብቃቱን አስመስክሯል።

ሁሉም ድሎች ቀላል አልነበሩም። ኃይሌ ከኤሚል ዛቶፔክና ላሴ ቬሮን በመቀጠል በአስር ሺ ሜትር ውጤታማ መሆን የቻለ ሶስተኛ ሰው ያደርገዋል። እአአ በ2000 በሲድኒ ኦሊምፒክ ከፖል ቴርጋት ጋር ያደረጉት ትንቅንቅ በታሪክ ከምን ጊዜውም ምርጥ የ10ሺ ሜትር ውድድሮች አንዱ ተደርጎ ይጠቀሳል። በሩጫ ህይወቱም 27 የማይታመኑ የዓለም ክብረወሰኖችን አሰመዝግቧል። ታዲያ ይህ ድንቅ አትሌት በሩጫ ዘመኑ ከደርዘን ጊዜ በላይ ስሙ በአትሌቲክስ ዊክሊይ ገጽ መታተሙ፤ ውድድር በቃኝ ካለ በኋላም ርዕስ እንደሆነ መቆየቱ ሲያንስበት እንጂ አይበዛበትም የሚሉ ቁጥራቸው ቀላል አይደለምና እኛም ለ50ኛ ዓመት የልደት በአሉ እንኳን አደረሰህ ብለናል።





# ዒድ ዓል-ፈጥር

**ሰላማዊት ውቤ**

ሰላም ልጆች! በተለይም የእስልምና እምነት ተከታይ ልጆች እንኳን ለዒድ አል-ፈጥር በዓል በሰላምና በጤና አደረሳችሁ!!! ልጆች፣ በዓሉ ጥሩ ነበር አይደል? እንዲህ እንደ ዒድ አል-ፈጥር ባሉ በዓላት ወቅት ብቻ የሚዘጋጁ ጣፋጭ ምግቦችን ከቤተሰብ ጋር ሰብሰብ ብሎ መመገብ፤ አዲስ ልብስ መልበስ፤ ከእማማና አባባ ጋር በመሆን በዓሉን ምክንያት አድርጎ ሽርሽር መሄድ፣ ወይም ዘመድ መጠየቅ ደስ ስለሚል ጥሩ ነበር እንደምትሉ እርግጠኛ ነኝ።

ልጆች ስለ እስልምና በዓላት አመጣጥና ታሪክ ምን ያህል ታውቃላችሁ? ስታከብሩት ስለ ታሪኩም ሆነ ስለ አመጣጡ ጠንቅቃችሁ አውቃችሁ ቢሆን የበለጠ የተሻለና የሚመረጥ ነው አይደል?

እናንተ ዛሬ በዚህ መልክ ግንዛቤ ኖሯችሁ በዓሉን ማክበራችሁ ነገ እናንተ ስታድጉና ትልቅ ሰው ስትሆኑ አሁን እናንተ ባላችሁበት እድሜ ደረጃ የሚተኩ ልጆች በዓሉን እያከበሩ እንዲያስቀጥሉ ያስችላል። በመሆኑም በጥሩ ሁኔታ ማክበራችሁ መልካም ነው። ስለዚህ፣ በዛሬው ጽሑፌ ስለ ዒድ ዓል-ፈጥር በዓል ትንሽ ግንዛቤ ላስጨብጣችሁ አስቤያለሁ።

ዒድ አል-ፈጥር በዓል በእስልምና እምነት ውስጥ በየዓመቱ ከሚከበሩ ሁለት ታላላቅ ክብረ በዓላት አንዱ ነው እሺ ልጆች።

ልጆች እንዳልኳችሁ በእስልምና እምነት ውስጥ በየዓመቱ የሚከበሩ ሁለት ታላላቅ ክብረ በዓላት አሉ። አንደኛው ከትናንት በስቲያ ያከበራችሁት ኢድ ዓል-ፈጥር በዓል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ኢድ አል አድሀ (አረፋ) በዓል ይሰኛል።

ልጆች ቢሆንም ዛሬ የምነግራችሁ ከትላንት በስቲያ ስላከበራችሁት የኢድ ዓል -ፈጥር በዓል ብቻ ነው። ሆኖም የዚህን በዓል ታሪክ ማወቅ ያለባችሁ የእስልምና ዕምነት ተከታይ ልጆች ብቻ ሳትሆኑ ክርስትናና ሌሎች ዕምነቶችን የምትከተሉ ልጆች በሙሉ ናችሁ። ምክንያቱም የአንዱን ዕምነት ታሪክ ሌሎቻችሁ ማወቃችሁ የዕውቀት አድማሳችሁን እንድታሰፉ ይረዳችኋል። ከዚህ በላይም ሰርክ አብራችሁ ትምህርት ቤት እንደምትሄዱት፤ አብራችሁ እንደምትጫወቱት ሁሉ በዓሉ ከሌሎች ሐይማኖት ዕምነት ተከታዮች ጋር ሥጋ ቢቀር ዳቦና ኬክ እየበላችሁና ለስላሳ እየጠጣችሁ፤ በአንድ ላይ የምታከብሩት በመሆኑ ስለበዓሉ ማወቅ ይገባችኋል።

ይሄን ከተገነዘባችሁ ስለ ኢድ አል ፈጥር በዓል ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ትንሽ ልንገራችሁ። ልጆች የኢድ አልፈጥር በዓል ዘንድሮ ለ1ሺህ 444ኛ ጊዜ ነው የሚከበረው። በዓሉ እንደ ረመዳን ሁሉ ሕዝበ ሙስሊሙ፣ በመተዛዘን፣ በመደጋገፍና በመረዳዳት፤ በፆምና በሶላት የሚያሳልፍበት የተቀደሰ ልዩ ወር ነው። ሰባት ዓመት የሞላቸው የእስልምና ዕምነት ተከታይ ልጆች በሙሉም በጾምና በጸሎቱ ይሳተፉበታል።

ኢድ አል ፈጥር የጾም ወቅት ማጠናቀቂያና መሸኛ ነው ተብሎ ይወሰዳል። በዓሉ በረመዳን ወር መጨረሻና በሸዋል ወር የመጀመርያ ቀን ላይ ይውላል።

በቅዱሱ የረመዳን ወር ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ሕዝበ ሙስሊሙ ራሱን ከምግብና መጠጥ በማቀብ በመልካምና በጎ ምግባር መትጋት ይጠበቅበታል። ልጆች፣ ለምሳሌ አንድ ዳቦ ለእናንተ ቢሰጣችሁ ግማሹን ቤተሰቡ ዳቦ ኖሮት ሊሰጠው ወይም ሊሰጣት ላልቻለው ጓደኛችሁ ማካፈል ማለት ነው። ወሩ የጾምና የመታዘዝ፤ የድካምና የመፈተን ወቅት ነው። ሆኖም ከሚበላባቸውና ከሚጠጣባቸው ወራቶች ሁሉ ቅዱሱ ወር የኢድ አል ፈጥር በዓል ወር ነው።

ልጆች የዒድ በዓል ከመከበሩ በፊት ባሉት የመጨረሻ ቀናት የእስልምና ዕምነት ተከታይ በሙሉ ዘካት አልፈጥርን ማውጣት እንዳለባቸውም ይነገራል። ልጆች ዘካት ምን እንደሆነ ትርጉሙን ታውቃላችሁ? አዎ፣ ዘካት ማለት ትላልቅ የእምነቱ አባቶች እንዲሁም የዕምነቱ ተከታዮች በሙሉ እንደሚናገሩት ለድሆች የሚሰጥ እርዳታ ማለት ነው። ድሀ ምን ዓይነት ነው ብትሉ ሁሉም በአቅሙ፣ ለምሳሌ በልብሱ፤ በሚበላው ነገር፤ በሌሎች መሰረታዊ የምንላቸው ነገሮች እኛ ካለን የኑሮ ደረጃ በእጅጉ የሚያንስ ማለት ነው። ልጆች ድሀ የሚባለው ማህበረሰብ የሚበላው የሌለው ብቻ ሳይሆን አካል ጉዳተኛና አቅመ ደካሞች፤ አረጋውያን፤ ህፃናት፤ እንዲሁም የተጎዱና የተገለሉ በተጨማሪም የእኛን ድጋፍ አጥብቀው የሚፈልጉ ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ሊሆኑ ይችላሉ። በመሆኑም ዘካት ከራስ በፊት ለሌላው ማሰብን የምንማርበት ስርዓትም ነው እሽ ልጆች። ስለዚህም የፈጥር ዘካ ከኢድ በፊት የግድ መከናወን ይኖርበታል። ልጆች እንደ ዒድ ያለውን የደስታ በዓል በሚገባ ለማጣጣም በዕድሜ ትንሽ ነን ወይም ትልልቆች ነን ሳንል ባለን አቅማችንና ባገኘነው ነገር ሁሉ ከእኛ በፊት መቅደም ያለባቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ሁሉ ማየት፣ መንከባከብና መደገፍ አለብን።



የዒድ በዓል ከአዲስ ጨረቃ መወለድ፤ ከአዲስ የንጋት ጀንበር መፈጠር፤ ከወርቃማ ጮራዎች መፈንጠቅ ጋርም የሚደመር ውብ በአል ነው። አዲስ ቀንና አዲስ ወር አድማሱ ላይ የበዓል ድባብ ይዘረጋል። ረመዳን ወር የፆም ፍቺና የኢድ አል-ፈጥር ሶላት በአብሮነትና በአንድነት በጀመአና አብሮነት ከምንም ጊዜ በላይ ይፈቅዳል፤ ይፈልጋል። በዓሉ ለብቻ አይከበርም። በየአካባቢው ያለውን ሁሉ ሕዝብ ሊሰበሰብ በሚችልበት ቦታ ላይ በጀምዐ በመስገድና ተክቢራ በማሰማት ነው የሚከበረው።

በመንደር፤ በሰፈርና በቤት ውስጥም ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት፣ ከወዳጅ ዘመድ በተጨማሪ ከሌሎች ዕምነት ተከታዮች ጋር በመሆን በሀላል ምግብና መጠጥ በዓሉን በደስታ ይከበራል። መልካም በዓል!!